





በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ፕላንና ልማት ቢሮ

የልማት መረጃ ስርአት አስ/ርና የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች ዘርፍ

የሥነ-ሕዝብና ልማት ዳይሬክቶሬት

የ5 ዓመት

(ከ2018 ዓ.ም እስከ 2022 ዓ.ም)

የሥነ-ሕዝብ ፕሮግራም ሰነድ

2018 ዓ/ም

ሚዛን-አማን

መዉጫ----------ገጽ

መግቢያ 1
ዓላማ 2
ክፍል አንድ 2
ጠቅላላ ሁኔታ 2
1.1 የክልሉ አጠቃላይ ገጽታ----------2
1.2. የሥነ-ሕዝብ አለም አቀፋዊ እና ሀገር አቀፋዊ ሁኔታ----------5
ክፍል ሁለት 7
2. የሥነ-ሕዝብና ልማት ነክ ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎች ዳሰሳ----------7
2.1. ብሔራዊ የሥነ-ህዝብ ፖሊሲ----------7
2.2. ብሔራዊ የጤና ፖሊሲ----------8
2.3. የሥነ-ተዋልዶ ጤና ስትራቴጂ----------8
2.4. ብሔራዊ የትምህርት ፖሊሲ----------8
2.5. ብሔራዊ ግብርና ገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂዎች----------9
2.6 ብሔራዊ የሴቶች ጉዳይ፤የወጣቶች እና የማህበራዊ ጥበቃ፤ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ፖሊሲ----------10
2.6.1 ብሔራዊ የሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ----------10
2.6.2 ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ----------11
2.7 ብሔራዊ የውሃ ሀብት ፖሊሲ----------13
ክፍል ሶስት 14
3. የክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ትንተና 14
3.1. የህዝብ ቁጥርና አሰፋፈር ሁኔታ ትንተና----------14
3.2. የሥነ-ሕዝብና ልማት ሁኔታ ትንተና----------15
3.2.1. የሥነ-ህዝብና አካባቢ ጥበቃ ሁኔታ 15
3.2.2. ሥነ-ሕዝብና ግብርና ሁኔታ 16
3.2.3. ሥነ-ሕዝብና የትምህርት ሁኔታ 17
3.2.3.1.4 *የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-12ኛ) ትምህርት* 19
3.2.3.1.5 *የሴቶች ትምህርት ተሳትፎ* 20

3.2.9. ሥነ-ሕዝብና የከተማ ልማት ሁኔታ.....22
3.2.10. ሥነ-ሕዝብና ንጹህ መጠጥ ውሃ ሁኔታ ትንተና.....23
3.2.12 ሥነ-ህዝብና ማህበራዊ ሁኔታ.....25
3.2.12.1 ሥነ-ህዝብና ሥርዓተ-ጾታ.....25
3.2.13. ሥነ-ሕዝብና የሥነ-ተዋልዶ ጤና ሁኔታ.....29
ክፍል አራት.....35
ክፍል አምስት.....37
5.ዓላማ፣ ስትራቴጂክ ጉዳዮች፣ ግቦችና የማስፈጸሚያ ስልቶች.....37
5.2. **ስትራቴጂክ ግቦች**----------37
5.3. **ስትራቴጂክ ግቦችና ዝርዝር ተግባራት**----------37
5.4 የማስፈጸሚያ ስልቶች.....47
5.5 ክትትልና ግምገማ.....48

መግቢያ

መንግስት የሀገሪቱንም ሆነ የክልሉን ህዝብ የኑሮ ሁኔታ ደረጃ በደረጃ ለማሻሻልና ፈጣንና ዘላቂ ልማት ዕውን ከማድረግ አኳያ ይፋ ካደረጋቸውና ተግባራዊ እየሆኑ ከሚገኙት የልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች አንዱ የብሄራዊ ሥነ-ህዝብ ፖሊሲ ነው፡፡ በ1985 ዓ.ም ይፋ የሆነው የፖሊሲው ዋና አላማ የህዝብ እድገት ምጣኔን ከኢኮኖሚ ልማትና ከተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ጋር እንዲጣጣም በማድረግ ከረጅም ጊዜ አኳያ የህዝብ የኑሮ ደረጃና አጠቃላይ ደህንነት እንዲሻሻል በማድረግ የሀገሪቱንና የክልሉን ህዝቦች ብልጽግና ማረጋገጥ ነው፡፡ ፖሊሲው ይፋ ከሆነ ወዲህ በክልላችን ከሥነ-ህዝብ አኳያ ሊከሰቱ የሚችሉ ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን በመረዳትና በሥነ-ህዝብ ጉዳዮች ላይ መስራት አማራጭ የሌለው መሆኑን በመገንዘብ ሥራውን ከሚመለከታቸው ሴክተር መ/ቤቶች ጋር የጋራ በመደረጉ በሁሉም የክልሉ ዞኖች፣ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ውጤታማ ሥራዎች ሲሰሩ ቆይቷል፡፡ በአጠቃላይ በየደረጃው የሚገኙ ባለድርሻ አካላት ባለፉት ዓመታት ለሥነ-ህዝብ ጉዳይ ተግባራት ባደረጉት ርብርብ የሥነ-ህዝብ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ለውጥ አስገኝቷል፡፡

በመሆኑም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የ5 ዓመት(ከ2018-2022 ዓ.ም) የሚተገበር የሥነ-ሕዝብ ፕሮግራም ሰነድ ለማዘጋጀት የሥነ-ህዝብ ጉዳዮችን በዋናነት ይፈፅማሉ ተብለው የክልሉ ሥነ-ህዝብ ምክር ቤት አባል የሆኑ 8 ሴክተር መ/ቤቶች ካዘጋጁዋቸው ዕቅዶች ውስጥ የሚካተቱና ከሥነ-ህዝብ ጉዳዮች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ተግባራት በተለይ በሥነ-ህዝብና ልማት ላይ የሚያተኩሩ 6 ስትራቴጂያዊ ግቦች ተለይተው ቀርቧል፡፡ ሰነዱ በ5 ክፍሎች የተከፋፈለ ሲሆን እንዲሚከተላዉ ተዘጋጅቷል፡፡

I. ዓላማ

በአጠቃላይ የሥነ-ህዝብ ፖሊሲን ዓላማ መነሻ በማድረግ ከ2018 ዓ.ም እስከ 2022 ዓ.ም የቀጣይ አምስት ዓመታት ዕቅድ የክልሉን የህዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔ ከክልሉ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት ምጣኔ እንዲሁም ከክልሉ የተፈጥሮ ሀብት ልማት አጠቃቀም ጋር በማጣጣም በሂደት የሕብረተሰቡን የኑሮ ደረጃና አጠቃላይ ደህንነት እንዲሻሻል ማድረግ ነው፡፡

ክፍል አንድ

1. ጠቅላላ ሁኔታ

1.1 የክልሉ አጠቃላይ ገጽታ

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በኢትዮጵያ 11ኛ ክልል ሆኖ 6 ዞኖችን በመያዝና 4 የክላስተር ዋና ከተሞችን በመያዝ ህዳር 14/2014 ዓ/ም የተመሰረተ ክልል ነው፡፡ ክልሉ በሰሜን አቅጣጫ ከኦሮሚያ ክልል፣ በምዕራብ በኩል ከጋምቤላ ክልል፣ በስተደቡብ በኩል ከደቡብ ሱዳን እና ደቡብ ኦሞ፣ በስተምስራቅ ከጎፋና ወላይታ ዞኖች፣ በስተሰሜን ምስራቅ ከምባታና ሀድያ ዞኖች ያዋስኑታል፡፡ ክልሉ በላቲትዩድ መስመር በ 50° 33’ እና 80° 31"N - በሎንግቲውድ መስመር 34° 88’ እና 38° 46’ E አቅጣጫ ላይ የሚገኝ ሲሆን አሁን ባለዉ አደረጃጀት በዉስጡ 6 ዞኖች ያሉት ሲሆን አጠቃላይ የቆዳ ስፋቱ 39,061.4 ስኩዌር ኪ/ሜ (3.91 ሚሊዮን ሄ/ር) እንደሚሆን ይገመታል፡፡

በኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት በ1999 ዓ.ም የተካሄደውን የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት ላይ ተመስርቶ በተካሄደ የህዝብ እድገት ትንበያ መሰረት በ2017 ዓ.ም የክልሉ የሕዝብ ብዛት 3,956,358 ደርሷል፡፡ ይህም ከጠቅላላው የሀገሪቱ ሕዝብ 111,652,998 አንጻር ሲሰላ 3.5 በመቶ ድርሻ አለው፡፡ ከዚህ ውስጥ ወንድ 1,974,457 (49.9%) ሴት 1,981,901 (50.1%) ድርሻ አላቸው፡፡ ከአጠቃላይ ሕዝብ ብዛት በገጠር 84.48% እና በከተማ 15.52% የሚኖሩ ሲሆን የህዝብ ጥግግቱ በአማካኝ በ1 ካሬ ኪ/ሜትር

መሬት 101 ሰዎች እንደሚኖሩ ይገመታል። ከጠቅላላው ህዝብ ከ15-64 ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ህዝብ ብዛት 1,964,624 (49.65%) መሆኑ ሲታይ በምርት ተግባር ላይ ሊሠማራ የሚችል አምራች ሃይል በበቂ ሁኔታ መኖሩን ያመላክታል። *(ምንጭ፡-ፓላንና ልማት ቢሮ 2017 ዓ.ም)*

የክልሉ መልከዓ-ምድራዊ አቀማመጥ ከባህር ወለል በላይ ከ348-3346 ሜትር ወሰን ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ የአየር ፀባዩ ለተለያዩ የግብርና ሥራዎች ምቹ ነው። አማካይ ዓመታዊ የዝናብ መጠን ከ400-2200 ሚ/ሜ ሲሆን የሙቀት መጠን ከ15.1°ሴ.ግ-27.5°ሴ.ግ ይደርሳል። ክልሉ ከሥነ-ምህዳራዊ ስብጥር አንፃር በረሃ 4.09%፣ ቆላ 56.50%፣ ወይናደጋ 33.51%፣ ደጋ 5.86% እና ዉርጭ 0.03% የአየር ፀባይ አለው።

በክልሉ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ያረጋገጠ አመቺና አሣታፊ የሆነ የፖለቲካ ሥርዓት ተዘርግቷል። የህብረተሰቡን ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን በማስጠበቅ ዕድገትና ልማትን ማምጣትና ሠላምን ማረጋገጥ በሚያስችል ሁኔታ መንግስታዊ መዋቅሩ የሕግ አውጪ፣ አስፈጻሚና ተርጓሚ አካላትን በመለየት ከክልል እስከ ቀበሌ አስተዳደር ድረስ ተደራጅቶ ሥራውን በማከናወን ላይ ይገኛል። ክልሉ በ6 ዞኖች፣በ41 ወረዳዎችና በ20 ከተማ አስተዳደር የተደራጀ ሲሆን የራሳቸዉ ቋንቋና ባህል ያላቸዉ 13 ብሔረሰቦች አሉት።የብሔረሰቦቹ ቋንቋ በሶስት የቋንቋ ቤተሰቦች ማለትም በኦሚዊ፣ናይሎ-ሰሀራዊ እና ኩሻዊ የሚመደቡ የባህልና የቋንቋ ብዝሀነት ያለው ሲሆን በክልሉ በርካታ ታሪካዊና ባህላዊ መስህቦች አሉት።ከእነዚህ ዉስጥ ዓለም አቀፍ እውቅና ካገኙ ብሔራዊ ፓርኮች ውስጥ የኦሞ እና የጨበራ ጩርጩራ ብሔራዊ ፓርኮች በካፋና በሸካ በተባበሩት መንግስታት የሳይንስ፣ የትምህርትና የባህል ድርጅት (በዩኔስኮ) የተመዘገቡ ለቱሪዝም ልማት ዕምቅ አቅም ያላቸው ባዮስፌር ሪዘርቮች ፣በዳዉሮ ዞን ሀላላ ኬላ ሎጅ፣በኮንታ ዞን ዳና ሎጅ፣በቤንች ሸኮ ዞን ደንቢ ሎጅ የሚገኙበት ሲሆን በተጨማሪም በሰዉ ሰራሽና በተፈጥሮ ያሉ በቀጣይ ተከልለዉ በፓርክነት ሊለሙ የሚችሉ በርካታ ስፍራዎች ይገኛሉ።

በክልሉ የሚገኙ ማህበራዊ ተቋማትን በተመለከተ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ከ1-8) 1,568 እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9-12 ብዛት 184 ሲሆን በግል ድርጅቶች የሚተዳደሩ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ከ1-8) 46 እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ከ9-12) 5 ተቋማት ተገንብተው ለህብረተሰቡ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። በክልሉ 2 ዩንቨርሲቲ 20 ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ 16 የግል ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች፣1 ግብርና ኮሌጅ፣1 መምህራን ትምህርት ኮሌጅ፣1 ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተቋማት ተገንብተው የተማረ ዜጋ ለሀገር እያበረከቱ ይገኛል *(ምንጭ፡- የፕላንና ልማት ቢሮ የ2017)*

የጤና ተቋማትና አገልግሎትን በተመለከተ አዳዲስ ተቋማትን ጨምሮ በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል 12 አጠቃላይ ሆስፒታል 4 የግል ሆስፒታል 4 እንዲሁም 129 ጤና ጣቢያዎች 807 ጤና ኬላዎችና 462 የግል ክሊኒኮች 4 የግል ጤና ጣቢያዎች ለህብረተሰቡ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። *(ምንጭ፡-2017 ዓ.ም የጤና ቢሮ መረጃ)*

በሀገሪቱ የተጀመረው የለውጥ እንቅስቃሴ ብዝሀ-መር የኢኮኖሚ ስርአት የተከተለ በመሆኑ ግብርና፤ቱሪዝም፣ማዕድንና የመሳሰሉት የክልሉ የኢኮኖሚ መሰረት ናቸው። በክልሉ የግብርና ዘርፍ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው የእርሻ ሥራ ሲሆን በዋነኛነት የሚመረቱ የአገዳና የብዕር ሰብሎች፣የተለያዩ ፍራፍሬዎች፣የስራስር ሰብሎች፣ ጥራጥሬዎች እንዲሁም ቡናና የተለያዩ ቅመማ-ቅመም ወዘተ.. ናቸው። የእንስሳት እርባታ ዘርፍም በከተማና ገጠር (በዶሮ እርባታ፤ንብ ማነብ፤ከብት ማድለብ..ወዘተ) እንዲሁም አርብቶ አደር አከባቢ የኑሮዋቸው መሰረት እንስሳት እርባታ በመሆኑ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል።

በአጠቃላይ ክልሉ ሰፋፊ የኢንቨስትመንት መሬት፤ አምራች የሰዉ ኃይል እና ለኢንዱስትሪ ምርት ግብዓት የሚሆኑ የግብርና ምርቶች እና ማዕድናት የታደለ ስለሆነ ልማታዊ ባለሃብቶች በየዘርፉ ቢሳተፉ ለራሳቸዉ ተጠቃሚ ከመሆናቸዉ በላይ ለአጠቃላይ ክልላዊና ሃገራዊ ዕድገት የበኩላቸዉን ሚና መጫወት ይችላሉ።

1.2. የሥነ-ሕዝብ አለም አቀፋዊ እና ሀገር አቀፋዊ ሁኔታ

የዓለም ህዝብ ቁጥር ከዓመት ወደ ዓመት በከፍተኛ ፍጥነት በመጨመር ምድር መሸከም ከምትችለው በላይ እየሆነ ስለመምጣቱ በመስኩ የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ፤20ኛው ክፍለ ዘመን ሳይንስና ቴክኖሎጂ በከፍተኛ ሁኔታ የተስፋፋበትና በብዙ የዓለም ሃገራት የኢኮኖሚ ዕድገት የታየበት ዘመን ቢሆንም ከህዝብ ቁጥር አኳያ ግን እጅግ ከፍተኛው የህዝብ ቁጥር የጨመረበት ክፍለ ዘመን ነበር።

እ.ኤ.አ.በ1800 የዓለም ህዝብ ቁጥር 950 ሚሊዮን የነበረ ሲሆን ከ100 ዓመታት ቆይታ በኋላ እ.ኤ.አ 1900 1.6 ቢሊዮን ሊደርስ ችሏል። እ.ኤ.አ በ1950 ቁጥሩ 2.51 ቢሊዮን በደረሰ ጊዜ የህዝብ ቁጥር የዕድገት ምጣኔው 1% ነበር። ከዚያ በኋላ እ.ኤ.አ. ከ1950 እስከ 1955 በነበሩት 5 ዓመታት የህዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔው 1.79% የደረሰ ሲሆን ይህ ምጣኔ በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመር እ.ኤ.አ. ከ1965 እስከ 1970 በነበሩት 5 ዓመታት 2.04% መድረሱን ጥናቶች ያመለክታሉ።

የዓለም ሕዝብ እ.ኤ.አ 1989 ቁጥሩ 5 ቢሊዮን፣ ከ10 ዓመታት በኋላ እ.ኤ.አ 1999፣ 6 ቢሊዮን እንዲሁም እ.ኤአ 2014 7 ቢሊዮን፤ እ.ኤ.አ በ2021 7.9 ቢሊየን የደረሰ ሲሆን በመቀጠል በየዓመቱ በአማካይ 79 ሚሊዮን ተጨማሪ ህዝብ በመጨመር እ.አ.አ በ2025 8.1 ቢልዮን የደረሰ ሲሆን እ.ኤ.አ በ2050 9.7 ቢሊዮን እንዲሁም እ.ኤ.አ 2100 11 ቢሊየን ሊደርስ እንደሚችል ሳይንሳዊ ትንበያዎች ያመላክታሉ።

ፈጣን የህዝብ ቁጥር ዕድገት ሥራ አጥነትን በማስፋፋት ቁጠባንና የነፍስ ወከፍ ገቢን በከፍተኛ ሁኔታ የሚጎዳ ከመሆኑም በላይ መንግስት ምርታማ በሆኑ ሥራዎች ላይ ከማተኮር ይልቅ እንደ መሰረተ ልማትና ማህበራዊ ተቋማት ወዘተ በማሟላት ሥራ ላይ እንዲያተኩር ስለሚገደድ ኢኮኖሚውን ክፉኛ እንደሚጎዳ ይታመናል።

በሃገራችንም የሚታየው የህዝብ ቁጥር ዕድገትና የሚያስከትለዉ ችግር ከዓለም ዓቀፍ ሁኔታ የተለየ አይደለም። እ.ኤ.አ በ1965 የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር 25 ሚሊዮን የነበረ ሲሆን እ.ኤ.አ በ1995 ከ30 ዓመታት በኋላ 57 ሚሊየን ቀጥሎ ከ20 ዓመታት በኋላ እ.ኤ.አ በ2015 100 ሚሊዮን የደረሰና በተደረገው ሳይንሳዊ ትንበያ መሰረት በአማካይ

2.66% በማደግ በ2025 እ.ኤ.አ 111 ሚሊዮን የደረሰ ሲሆን ከ26 ዓመታት በኋላ እ.ኤ.አ በ2050 190 ሚሊየን ሊደርስ እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ *(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ሥታትስቲክስ አገልግሎት)*

ከቀረበው መረጃ በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው የሀገሪቱ ህዝብ ቁጥር ከ25 ዓመታት ባነሰ ጊዜ በእጥፍ የሚያድግ በመሆኑ በተጨማሪ እ.ኤ.አ በ1995 እና እ.ኤ.አ በ2024 የተወለደው የኢትዮጵያ የህዝብ ቁጥር 52 ሚሊየን መሆኑ ሲታይ በጣም ከፍተኛ የውልደት መጠን መኖሩን የሚያመለክት ስለሆነ ይህንን ህዝብ በልማት አቅጣጫ በመምራት ወደ እድል መቀየር ያስፈልጋል፡፡ ምንም እንኳን በሀገር ደረጃ በ1985 ዓ.ም ጸድቆ ሲተገበር የቆየው ብሔራዊ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ ክለሳ የሚያስፈልገው ቢሆንም ፖሊሲው ተግባራዊ በተደረገባቸው ዓመታት ከሁለንተናዊ ዕድገት አኳያ ትልቅ ለውጥ የታየበት ነበር፡፡

ክፍል ሁለት

2. የሥነ-ሕዝብና ልማት ነክ ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎች ዳሰሳ

2.1. ብሔራዊ የሥነ-ህዝብ ፖሊሲ

በማሕበራዊ ምጣኔ ሐብት ልማትና በሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔ መካከል ያለውን ልዩነት ለማጥበብ እንዲረዱ ታስበው ከተነደፉት ብሔራዊ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎች መካከል በ1985 ዓ.ም ይፋ የሆነው የብሔራዊ ሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ ለአብነት ይጠቀሳል፡፡

ብሔራዊ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ ዋና ዓላማ በኢትዮጵያ እየታየ ያለውን ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔ በመቀነስ ከምጣኔ ሐብቱ ልማትና የተፈጥሮ ሐብት አጠቃቀም ጋር ተጣጥሞ እንዲያድግ በማስቻል በቀጣይ ጊዜያት የሕዝቡን የኑሮ ሁኔታ ደረጃ በደረጃ በማሻሻል ዜጎች የተሻለ ኑሮ እንዲኖሩ ማስቻል እንደሆነ ያስረዳል፡፡ ዓመታዊ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔው ከፍተኛ መሆን፣ የምጣኔ ሐብት ልማቱ አዝጋሚ መሆንና ግድ-የለሽ የተፈጥሮ ሐብት አጠቃቀማችን የመነጨው የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች በተለይ የድሕነት ቀናሽ ሴክተሮች የልማት ዕቅዶች ውስጥ በሚገባ ተካትተው አለመተግበራቸው መሆኑ በፖሊሲው ሰነድ ውስጥ ተብራርቷል፡፡

ብሔራዊ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲው በጥቅሉ ሲታይ የአገሪቱን ሁለንተናዊ ልማት በማፋጠን ለፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔ ምክንያት የሆነውን አጠቃላይ የውልደት መጠንን ደረጃ በደረጃ በመቀነስ በማሕበራዊ ምጣኔ ሐብት ልማትና በሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔ መካከል ያለውን ልዩነት በማጥበብ የዜጎችን የኑሮ ደረጃ በማሻሻል ለአደጋ በቀላሉ ተጋላጭ የሆኑትን የእናቶችንና ሕጻናትን ሕመምና ሞት በከፍተኛ ሁኔታ በመቀነስ ዘላቂ ልማትን ዕውን ማድረግ እንደሚቻል ያስረዳል፡፡ ፖሊሲዉን መነሻ በማድረግና ግቡን ለማሳካት የ5 ዓመት የሥነ-ሕዝብ ፕሮግራም አዉንታዊ ድርሻዉ የጎላ ነዉ፡፡

2.2. ብሔራዊ የጤና ፖሊሲ

በ2016 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣዉ አዲሱ ብሔራዊ የጤና ፖሊሲ ጤናን በማበልጸግና በሽታን በመከላከል ላይ ያተኮረ በየደረጃው ያለውን አጠቃላይ የጤና አገልግሎት ለሁሉም ይበልጥ ተደራሽ የሚያደርግ፤ድንገተኛ አደጋዎችን መቋቋም የሚችል፤ የማይበገር የጤና ሥርዓት እንዲገነባ ለማድረግ ሲሆን በተለይም የጤና አገልግሎት ተደራሽነት፣ጥራት፣ፍትሐዊነት፣የህብረተሰቡን ተሣትፎና ባለቤትነትን እና ራስን የመቻል መርህን፣የዘርፎች ትብብርን፣ የግሉ ዘርፍ እና የሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ተሳትፎ ግንዛቤ ዉስጥ በማስገባት የተቃኘ መሆኑና ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ በሽታዎችን በመቆጣጠር 'አንድ ጤና' (One Health) ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የሕዝቡን ጤና ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ ነው።*(ብሔራዊ የጤና ፖሊሲ 2016 ዓ.ም)*

2.3. የሥነ-ተዋልዶ ጤና ስትራቴጂ

የሥነ ተዋልዶ ጤና ስትራቴጂ የብሔራዊ ጤና ፖሊሲውን መርህ ተከትሎ የተነደፈ ሲሆን በዋናነት የሚያተኩርባቸው ጉዳዮች፡- ለወንዶች፣ ለሴቶች፣ ለወጣቶች፣እና ለጎልማሶች የስነ ተዋልዶ ጤና መብትና ፍላጎት መልስ መስጠት፤ለስነ-ተዋልዶ ጤናና ለጤናማ የወሲብ ባህርያት ምቹ ሁኔታን መፍጠር፤ ጤናማ የሆነ እርግዝናን ከማረጋገጥም በላይ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተደራሽነትና ተጠቃሚነት እንዲጨምር ማድረግ፣ እንደ ጾታ መድሎና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የመሳሰሉ የማህበራዊና ባህላዊ ልማዶች በስነ ተዋልዶ ጤና ላይ ያላቸውን አሉታዊ ተጽእኖ መቀነስ በስትራቴጂው ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው።

2.4. ብሔራዊ የትምህርት ፖሊሲ

የካቲት 2015 ዓ.ም.የተሻሻለው የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ዋነኛ ዓላማ ጥራት ያለው ትምህርትና ሥልጠና በተለይም ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ መካከለኛ ደረጃ ነፃና የግዴታ ትምህርት በተስማሚ ቴክኖሎጂ በማስደገፍ ለሁሉም በማዳረስ የግለሰብን አዕምሮአዊ፣አካላዊ፣ማህበራዊ፣መንፈሣዊ እንዲሁም መልካም እሴቶችን ማጐልበት፣

ትምህርትና ሥልጠናን ከግለሰባዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ እንዲሁም ከኢንዱስትሪና ከግብርና ለውጥና እድገት ጋር ማስተሳሰር፣ለነባራዊ ሁኔታዎች ምላሽ የሚሰጡና ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚ ማልማትን ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር ኢኮሚኖሚውን የሚያሳድጉ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ ብቁ ዜጐችን ማፍራት፣ትምህርትና ሥልጠናን ከግለሰባዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ እንዲሁም ከኢንዱስትሪና ከግብርና ለውጥና እድገት ጋር ማስተሳሰር፣የኢትዮጵያን መልካም ባህል የሚያበለጽጉ፤የሀገር ፍቅር ያላቸው፣ ብዙሃነትን የሚቀበሉ፣ ሰብአዊ መብቶችን የሚያከብሩ፣ ለሰው ልጅ ደህንነትና እኩልነት፣ለፍትሕ፣ለሠላም ዘብ የሚቆሙ፣ በግብረገብ፣ በሥነ ምግባርና በዴሞክራሲ ባህል የታነጹ፣የሀገራቸውን ታሪክ የሚያውቁ፣ለሀገራቸው አንድነት ዘብ የሚቆሙ፣ለሕዝብና ለሀገር ፍቅር ያላቸው ሁለንተናዊ ሰብእናቸው የተሟላ ዜጐችን ማፍራት፣ በራሳቸው የሚተማመኑ፣ እውነትን የሚሹ፣ ለእውነት የሚቆሙ፣ በምክንያታዊ ትንተናና በውይይት የሚያምኑ፣ በሙያቸው ብቃት ያላቸው፣ ሥራ ፈጣሪዎች፣አዳዲስ ግኝቶችን የሚያፈልቁ፣ ውበትን የሚያደንቁ፣ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ እንዲሁም ለሀገር በቀል እውቀት መስፋፋት፣ መስረጽና ማደግ የሚተጉ፤ በዚህም የመመራመርና የማመዛዘን ብቃታቸውን የሚያጐለብቱ እና ለሕግ ዘብ የሚቆሙ ዜጐችን ማፍራት የሚሉ ጉዳዮችን ፖሊሲዉ አካትቶ ይዟል። (ትምህርት ፖሊሲ 2015፤ ገጽ 6)

2.5. ብሔራዊ ግብርና ገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂዎች

በ2014 ዓ.ም የተሻሻለዉ ብሔራዊ የገጠር ልማት ፖሊሲ ትኩረቱ ፈጣን የግብርና ምርትና ምርታማነት እድገት ማረጋገጥ፣የአነስተኛ ይዞታ አርሶና አርብቶ አደር ግብርናን በገበያ ተወዳዳሪነት ማሳደግ፣የተፈጥሮ ሃብት ልማትና ጥበቃን በማሻሻል ዘላቂ አጠቃቀምን ማሳደግ፤የደን ልማትና አጠቃቀም በማሳደግ ሀገራዊ የደን ውጤትን ፍላጎት ማሟላት፣በገጠር የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን በማስፋፋት የስራ እድል ፈጠራን ማሳደግ፣በከተማና ከተማ ዙሪያ በንዕዕር ከፍተኛ ምርታማነትና ዋጋ ያላቸው የግብርና ልማት ማሳደግ አንዲሁም በአየር ንብረትና በሌሎች የተፈጥሮ ክስተቶች ተዕዕኖ የሚመጣ ተጋላጭነትን መቋቋም የሚያስችል አቅም ማሳደግ ናቸው። ፖሊሲዉ

ካስቀመጠቸዉ የትኩረት አቅጣጫዎች ዉስጥ አንዱ የገጠሩን ማህበረሰብ የኤክስቴንሽን እና ምክር አገልግሎት የተለያዩ ተጠቃሚዎችን የእውቀት፣ክህሎት፣ የአመለካከትና የባህሪ ለውጥ ለማምጣት የተለያዩ የኤክስቴንሽን ዘዴዎችና ሥልቶችን በመጠቀም የማስተማር፣ የማማከር፣ የማደራጀትና የማስተባበር አገልግሎት መስጠት። ይህንን አገልግሎት ገበያ ተኮር፣ ምሉዕ፣ ተደራሽ፣ ዘላቂ፣ አሳታፊ እና ፍላጐት ላይ መሠረት ያደረገ የግብርና ልማትን በማሳካት የተጠቃሚውን ህይወት ማሻሻልና ለሀገር ኢኮኖሚ አስተዋጽኦ የሚያደረግ ቁልፍ መሣሪያ እንደሆነ አስቀምጧል። በሌላ በኩል ተፈጥሮ ሀብትን በማልማትና በመንከባከብ ላይ ያተኮረ የእጽዋት ሽፋንንና ስብጥርን የማሻሻል፣የመሬት መራቆትን እና የአፈር መሸርሸር በመቀነስ፣የአፈር ጤንነትና ለምነት በመጠበቅና በማሻሻል የግብርና ግብአቶች ውጤታማነትን በማረጋገጥ እንዲሁም የገፀ እና ከርሰ-ምድር ውሃን በማበልፀግ ለዘላቂ የግብርና ልማት መሰረት እንደሚጥል፤በአጠቃላይ የተፈጥሮ ሃብት ልማትና ጥበቃ ጤናማ አካባቢን በመፍጠር፣ ዘላቂ የግብርና ልማት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ የምግብና ስነ-ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ወሳኝ ድርሻ እንዳለዉ በፖሊሲዉ ተጠቅሷል። *(የተሻሻለዉ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ 2014)*

2.6 ብሔራዊ የሴቶች ጉዳይ፤የወጣቶች እና የማህበራዊ ጥበቃ፤ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ፖሊሲ

2.6.1 *ብሔራዊ የሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ*

በሀገራችን የኢፌድሪን ሕገ መንግስት ልዩ ትኩረት ከሰጣቸው ሥነ ህዝብ ነክ ጉዳዮች መካከል አንዱ የሴቶች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መብቶችን በማስጠበቅ ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ ያወጣው ድንጋጌ ነው። በኢኮኖሚያዊ ዕድገት እና ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በሚገኘው የህዝብ ቁጥር ዕድገት መካከል ያለውን ክፍተት በማጥበብ፤የሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች የኑሮ ደረጃ በማሻሻልና በቀላሉ ለአደጋ ተጋላጭ የሚሆኑትን የእናቶችንና ሕፃናትን የሕመምና ሞት መጠን በከፍተኛ ሁኔታ በመቀነስ ዘላቂ ልማትን ዕውን ማድረግ እንደሚቻል ያስረዳል።

ብሔራዊ የሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ ዋና ዋና ዓላማዎች ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፡ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ ህጻናት፣ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን በሀገሪቱ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤የሰብአዊ መብቶችን ማስከበር፡ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ከመገለል፣ ከጥቃትና ከበደል ነፃ ሆነው የሚኖሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤ድህነትን መቀነስ፡ ማህበራዊ ጥበቃን በማስፋፋት ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች ራሳቸውን እንዲችሉና ከድህነት ወለል በላይ እንዲወጡ መደገፍ፤ማህበራዊ ደህንነትን ማስፈን፡ ጠንካራ ማህበራዊ መስተጋብርና ቤተሰባዊ ትስስር እንዲኖር በማድረግ የተረጋጋ ማህበረሰብ መገንባት ሲሆን ከትኩረት አቅጣጫዎች ውስጥ፡- የሴቶች ጉዳይ ኢኮኖሚያዊ አቅምን ማሳደግ፤ ሴቶች የንብረትና የፋይናንስ ባለቤት እንዲሆኑ ማበረታታት፤ፖለቲካዊ ውሳኔ ሰጪነት፡ ሴቶች በከፍተኛ አመራርና ውሳኔ ሰጪነት ደረጃ ላይ ያላቸውን ቁጥር ማሳደግ፤ጎጂ ልማዶችን መዋጋት፡ እንደ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ ግርዛት እና ጾታዊ ጥቃቶችን በህግና በግንዛቤ መከላከል፤ የህጻናትና ወጣቶች ደህንነት ህጻናት ከአካልና ከመንፈስ ጥቃት ተጠብቀው እንዲያድጉ ማድረግ፤የወጣቶችን የስራ አጥነት ችግር ለመፍታት የሚያስችሉ የክህሎትና የስራ እድል ፈጠራ ስራዎች ማሳደግና አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን አካታችነት (Inclusion)፡ መሰረተ ልማቶች፣ የስራ ቦታዎችና ትምህርት ቤቶች ለአካል ጉዳተኞች ምቹ እንዲሆኑ ማድረግ፤ የአረጋውያንን እውቀትና ልምድ ለትውልድ ማስተላለፍና ተገቢውን ክብካቤና ድጋፍ ማግኘት የሚችሉበትን ስርዓት መዘርጋት፤ማህበራዊ ጥበቃ (Social Protection) ድንገተኛ አደጋ ለሚደርስባቸውና በጣም ለተቸገሩ ዜጎች የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ የሚሰጥበትን የደህንነት መረብ ፕሮግራም ማጠናከርና የጎዳና ተዳዳሪነትን መቀነስና ማህበራዊ ተሀድሶ መስጠት የሚሉ አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡ (www.mowsa.gov.et)

2.6.2 *ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ*

በ2016 ዓ.ም የተሻሻለው ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ በኢትዮጵያ የሚገኙ ወጣቶችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፣ በሀገሪቱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ

እንቅስቃሴዎች ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ ታቅዶ የተዘጋጀ ሰነድ ነው። ዓላማዉም ወጣቱ በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፣በሰላም፣እና በልማት ሥራዎች ላይ በንቃትና በባለቤትነት እንዲሳተፍ ማድረግ እንዲሁም ከልማቱ ፍሬ ተጠቃሚ እንዲሆን ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ነው። ከፖሊሲዉ ትኩረት አቅጣጫዎች ዉስጥ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት፦ የወጣቶችን የሥራ አጥነት ችግር ለመቅረፍ የሥራ ዕድል ፈጠራን ማፋጠን፣ የሥራ ፈጠራ ክህሎትን ማሳደግ እና የፋይናንስ አቅርቦትን ማመቻቸት፤ትምህርትና ሥልጠና፦ የትምህርት ጥራትን ማሻሻል እና ትምህርቱ ከገበያው ፍላጎት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ማድረግ (በተለይ በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ)፤ጤናና ደህንነት፦ የወጣቶችን ስነ-ተዋልዶ ጤና መጠበቅ፣ ከአደንዛዥ ዕፅ ሱስ መከላከል እና የአዕምሮ ጤና አገልግሎቶችን ተደራሽ ማድረግ፤ፖለቲካዊ ተሳትፎ፦ ወጣቶች በውሳኔ ሰጪነት ደረጃ እንዲሳተፉ እና በየደረጃው ባሉ የአመራር እርከኖች ውስጥ እንዲካተቱ ማበረታታት እንዲሁም በጎ ፈቃደኝነት፦ ወጣቶች በበጎ ፈቃድ አገልግሎት አማካኝነት ለሀገር ግንባታ አስተዋጽኦ የሚያደርጉበትን ሥርዓት መዘርጋት የሚሉ ተካተዋል። (https://www.mowsa.gov.et)

2.6.3 *ብሔራዊ የማህበራዊ ጥበቃ፤ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ፖሊሲ ሰነድ*

በፖሊሲው ልዩ ትኩረት ከተሰጣቸው የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የተጋለጡ በተለይም በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ህጻናት፣ ሴቶች፣አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ ሰርቶ ለማደር ጉልበትና አቅም የሌላቸው ግለሰቦች፣ ስራ አጦችና በተለያዩ የማህበራዊ የተፈጥሮና ሌሎች ምክንያቶች ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ዜጎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በሥራ ምክንያት የሚከሰቱ አደጋዎችንና የጤና ጠንቆችን በመቆጣጠር ሰብአዊ ጉዳቶች እንዳይከሰቱ በማድረግ የሠራተኞችን ምርታማነት ለማሳደግ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መከላከል በመሆኑ በሥራ ቦታ የመከላከል ባህልን ለማሳደግ የሚያስችሉ ሰፊ የግንዛቤና የአቅም ግንባታ ተግባራትን በማከናወን እና የሚመለከታቸውን አካላት ትብብርና ቅንጅት በማጎልበት እንዲሁም የቁጥጥር ሥርዓቱን በማጠናከር ላይ ያተኮረ እንቅስቃሴ ማድረግ ፤ሴቶች፣ ወጣቶች እና የአካል ጉዳት ያለባቸው ሠራተኞች የሥራ ሁኔታዎች እንዲሻሻሉ እና

የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ ደረጃ በደረጃ እንዲወገድ ማድረግ፤ የሥራ ቦታ ኤች አይ ቪ እና ኤድስ ምላሽ ከሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት ጋር ተቀናጅቶ እንዲካሄድ ማድረግ፤ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎቶች የአካባቢ ጥበቃን እና ከብክለትና ከብክነት የፀዳ የአሰራር ዘዴን ታሳቢ ያደረጉ እንዲሆኑ ማድረግ፤ የሚሉት የትኩረት አቅጣጮች በፖሊሲዉ ተካቷል። (ብሔራዊ የሙያና ደህንነትና ጤንነት ፖሊሲ 2006 ዓም)

2.7 ብሔራዊ የውሃ ሀብት ፖሊሲ

በ2016 ዓ.ም በድጋሚ የጸደቀዉ የውሃ ሀብት ብሔራዊ ፖሊሲና ግብ በዋነኛነት ትኩረት ያደረገው የሀገሪቱን የውሃ ሀብት በዘላቂነት ለጠቅላላው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት በብቃት፣ በፍትሃዊነት እና በተሻለ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውልና እንዲመራ ሁሉንም ሀገራዊ ጥረቶች መምራት እና ማስተባበር፤የውሃ ሀብት ልማት እና አስተዳደር ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ልማት አስተዋጽኦ ማድረጉን እና የአየር ንብረት ለውጥ መላመድ ስራዎች በማንኛውም የውሃ ዘርፍ ልማት ውስጥ መካተታቸውን ማረጋገጥ ነዉ።

በፖሊሲዉ ካስቀመጠዉ የትኩረት አቅጣጫዎች ዉስጥ የውሃ ሀብት ልማት፣ አጠቃቀም እና ጥበቃ ተነጣጥለው የማይታዩ መሆናቸውን በመገንዘብ፤ የውሃ አቅርቦት እና ሳኒቴሽን፣ መስኖ እና ፍሳሽ ማስወገጃ እንዲሁም የውሃ ግንባታዎች (hydraulic structures)፣የተፋሰስ ልማት እና ተያያዥ ተግባራት ተቀናጅተው በአንድነት እንዲከናወኑ ማድረግ አንዲሁም ውጤታማ እና ዘላቂ የውሃ ሀብት አጠቃቀም እና አስተዳደርን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ የቁጥጥር ማዕቀፎችን በመውሰድ የጎርፍ አደጋን መከላከልና መቆጣጠር፤የውሃ ሀብትንና አጠቃላይ የውሃ አከባቢን በዘለቄታዊ መንገድ መንከባከብ፣መጠበቅና ማጎልበት እንዳለበት በግልጽ አስቀምጧል። (ብሔራዊ የዉሃ ፖሊሲ)

ክፍል ሶስት

3. የክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ትንተና

3.1. የህዝብ ቁጥርና አሰፋፈር ሁኔታ ትንተና

የ1999 ዓ.ም የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤትን መሰረት በማድረግ በተደረገው ትንበያ በ2017 ዓ.ም የክልሉ ህዝብ ብዛት 3,956,358 እንደሚሆን ሲገመት ከዚህ ውስጥ ወንድ 1,974,457 (49.9%) እና ሴት 1,981,901 (50.1%) ድርሻ አላቸው። ከአጠቃላይ ሕዝብ ብዛት በገጠር 84.48% እና በከተማ 15.52% የሚኖሩ ሲሆን የህዝብ ጥግግቱ በአማካኝ በ1 ካሬ ኪ/ሜትር መሬት 101 ሰዎች እንደሚኖሩ ይገመታል። የክልሉ ህዝብ የእድሜ ስብጥር እንደሚያሳየዉ ከአጠቃላይ ህዝብ ቁጥር ከ0-14 እድሜ ክልል 1,909,051(48.25%)፣ከ15-29 እድሜ ክልል 1,112,164(28.11%) ከ30-64 እድሜ ክልል 852,460(21.54%)፣ከ64 አመት በላይ እድሜ ክልል 82,683(2.08%) በአጠቃላይ 3,021,214 (76.36%) ያህሉ ከ0-29 እድሜ ያሉ ህጻናት እና ወጣቶች መሆኑ ሲታይ ለወደፊት የመዋለድ አቅሙ በጣም ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል።ይህንን ሀይል በሚገባ ማስተማር እና በቤተሰብ እቅድ ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር ካልተቻለ ለክልሉ የሕዝብ ቁጥር መጨመር እንደምክንያት ሁኖ ይቀጥላል። ከጠቅላላው የህዝብ ቁጥር ከ15-64 ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ህዝብ ብዛት 1,964,624 (49.65%) መሆኑ ሲታይ በምርት ተግባር ላይ ሊሠማራ የሚችል የልማት ሃይል በበቂ ሁኔታ መኖሩን ያመላክታል። የእድሜ ጥገኝነት ሁኔታ በተመለከተ ከ15 አመት በታች እና ከ64 አመት በላይ የሆነዉ ህዝብ ቁጥር ከአጠቃላይዩ ህዝብ 1,991,734(50.34%)መሆኑ ሲታይ የእድሜ ጥገኝነት ምጣኔዉ ከፍተኛ በመሆኑ አምራች ኃይሉን በሚገባ ተጠቅሞ ለልማት ማዋል ካልተቻለ ለክልሉ ተጨማሪ ጫና ሆኖ የሚቀጥል ይሆናል።

በአጠቃላይ የክልሉ የህዝብ ዕድገት ምጣኔ በ2017 ዓ/ም 3.11% መድረሱ ሲታይ የሥነ-ህዝብ ችግሮችን በተለይም የህዝብ ቁጥር ዕድገትን ከኢኮኖሚ ልማት ጋር ከማጣጣም አንፃር ሰፊ ሥራ መሰራት እንዳለበትና በሌሎችም ዘርፎች ለምሳሌ በደን ተከላና አካባቢ ጥበቃ፣በእናቶችና ህፃናት ጤና አጠባበቅ፣ሴት ልጆችን ከማስተማርና

በኢኮኖሚ በማህበራዊና ፖለቲካዊ ዘርፎች ያላቸውን ተሳትፎ ከማሳደግና ተጠቃሚነታቸውን ከማረጋገጥ እንደዚሁም፤ማህበራዊ ድጋፍና ጥበቃ የሚያስፈልጋቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ከመደገፍና ማህበራዊ ጠንቆችንም ከመዋጋት ወዘተ አንፃር ትልቅ ትኩረት የሚፈልግ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ (ፕላንና ልማት ቢሮ 2017)

3.2. የሥነ-ሕዝብና ልማት ሁኔታ ትንተና

3.2.1. የሥነ-ህዝብና አካባቢ ጥበቃ ሁኔታ

የብዝሀ ሕይወት ሀብት ለግብርና፣ ለጤና፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለአካባቢ ጥበቃ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ መላመድና መቋቋም፣ ለኢንቨስትመንት እንዲሁም የተረጋጋ ህብረተሰብ ለመፍጠር በአጠቃላይ ለሌሎች የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች ከፍተኛ ሚና አለው፡፡

ክልሉ ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት አላቸው ከሚባሉ የኢትዮጵያ ክልሎች አንዱ ሲሆን የተፈጥሮ አካባቢ ሁኔታን ስንመለከት የተሻለ የደን ሀብት፣ ለም አፈር፣ ከውርጭ እስከ በረሀማ የአየር ንብረት፣በርካታ የዱር እንስሳት፣ከፍተኛ የሆነ የውሀ ሀብትና ሌሎች የተፈጥሮ ሀብት በውስጡ አካቶ በመያዝ የሚታወቅ ነው፡፡

በክልላችን ከፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር ተያይዞ በአንድንድ አከባቢ እየተከሰተ ያለውን ከፍተኛ የሆነ የተፈጥሮ ሀብት ውድመትን ለመቀነስ በሥነ-ሕዝብና አካባቢ ልማት ዙሪያ የሕዝቡን ግንዘቤ በማሳደግ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ቢሆንም በቀጣይ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡ የደንና የደን ሀብታችን ለአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ መሳካትና በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ እየታየ ያለውን የሙቀት አማቂ ጋዝን በመቀነስ ረገድ ያለውን ፋይዳ ከግንዛቤ በማስገባት በተሰራዉ ሥራ የደን ሽፋን በ2017 ዓ.ም 43.85 ደርሷል፡፡ በቀጣይ ሽፋኑን በማሳደግና በአግባቡ በመጠበቅ የደኑን ሚና ከፍ በማድረግ የአካባቢውን የአየር ንብርት ለውጥ እንዳይከሰት ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል፡፡ *(ደንና አከባቢ ጥበቃ ቢሮ ሪፖርት 2017)*

በክልላችን የተፈጥሮ አካባቢ በተለይም የደን ሽፋን ባለበት ተጠብቆ እንዳይቆይ ምክንያት ከሚሆኑት ውስጥ የማገዶ እንጨት ፍጆታ መጨመር፤የእርሻ ማሳ ፍላጎት

መጨመርና ለመኖሪያ ቤት ግንባታ ሲባል የሚቆረጠው እንጨት ወዘተ...የሚጠቀሱ ናቸው። ስለሆነም ያሉ የቴክኖሎጂ አማራጮችን በመጠቀም ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎችን ማስፋፋትና የኤሌክትሪክ አጠቃቀምን በማሳደግ፤የኑሮ መሰረታቸዉ በደን ዉጤቶች ላይ ያተኮሩ የህብረተሰብ ክፍሎች አማራጭ የሥራ ዕድል በመፍጠርና ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ ሊያመጡ የሚችሉ ጉዳዮች ላይ ህብረተሰቡ ግንዛቤ ኖሮት እንዲጠቀም ባለድርሻ አካላት ጋር ትኩረት በመስጠት ሊሰራበት ይገባል።

3.2.2. ሥነ-ሕዝብና ግብርና ሁኔታ

የግብርና ዘርፍ በሀገሪቱ ብሎም በክልሉ ኢኮኖሚ እድገትና ድህነትን በመቀነስ ረገድ ባለው ወሳኝ ድርሻ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ዘርፍ መሆኑ ይታወቃል። ዘርፉ የሚጠበቅበትን ውጤት ለማሳካት የተነደፉ ሀገራዊ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ለማሳካት በየወቅቱ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን በማቅረብና የውሃ ሀብታችንን በላቀ ደረጃ በመጠቀም ዉጤታማ ሥራ መስራት ይጠበቃል። በመሆኑም በክልላችን ሰፊ አቅም ያለው ዘርፍ ግብርና ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በዋና ዋና ሰብሎች ላይ ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ አንጻር በ2016/2017 ዓ.ም በአዝርዕት ሰብሎች በመኸር፣ በበጋ መስኖ እና በበልግ ወቅት አጠቃላይ 745,090.5 ሄ/ር ማሳ በዘር በመሸፈን 20,632,359 ኩ/ል(100%+) ምርት ለመሰብሰብ ተችሏል።በተጨማሪም በምርት ዘመኑ አጠቃላይ በሆርቲካልቸር ሰብሎች በአትክልት፣ሥራሥር፣እንሰትና ፍራፍሬ በበልግ መስኖና መኸር አዝመራ 326,698 ሄ/ር በማልማት 66,958,777 (97.6%) ኩ/ል ምርት ማግኘት ተችሏል። የቡና፣ሻይ ቅመማ ቅመም ምርቶችን በተሻለ ጥራትና ብዛት እንዲሁም የገበያ ትስስርን በመፍጠር ለማዕከላዊ ገበያ በማቅረብ ለአገር ኢኮኖሚ ዕድገት የበኩሉን እንዲያበረክት በማድረግ ረገድ በ2017 ዓ.ም ለማዕከላዊ ገበያ የቀረበ የታጠበና ያልታጠበ ቡና በቶን 48,153፤ቅመማቅመም በቶን 56,170 እና የሻይ ምርት ለሀገር ውስጥና ለዉጪ ገበያ 6,215.6 ቶን፤ የአከባቢን ስነ-ምህዳር በመጠበቅ የግብርናን ምርታማነት ከማሳደግ አንጻር 213,187 ሄ/ር በተፋሰስ ሥራ መልማት ተችሏል፤በበጋ መስኖ ስራ የተለያዩ የዉሃ አማራጮችን በመጠቀም አርሶ እና አርብቶ አደሮች የበጋ መስኖ ስራ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል በ2017 ዓ.ም 5,017 በሄ/ር በማልማት

ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል። የክልሉን የእንስሳት ሀብት በመጠቀም 69,459 ቶን የሥጋ ምርት ማግኘት ተችሏል። *(ግብርና ቢሮ ሪፖርት 2017)*

በአጠቃላይ ከሀገራዊና ክልላዊ ዕቅድ አኳያ ግብርናው ለኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ግብዓቶችን የማቅረብና የዉጪ ምንዛሬ ማስገኛ ምርት የማምረት ሚናዉን እንዲወጣ በዘርፉ ምርታማነትን በላቀ ደረጃ ለማሳደግ የሚያስችሉ የግብአት አቅርቦት፤ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማጎልበት፤የመስኖ ሥራዎችን ማስፋፋት ፤ ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የተሰጠውን ትኩረት አጠናክሮ ማስቀጠል፤ የኤክስፖርት ምርቶችን በዓይነት፣በጥራትና በመጠን ማሻሻልና የህብረት ሥራ ማህበራትን የገበያ ድርሻ ማሳደግ በትኩረት ሊሠራበት ይገባል።

ይህም የህብረተሰቡን ኑሮ በማሻሻል የምግብ ዋስትናን በቤተሰብ ደረጃ በማረጋገጥ የህዝብ ቁጥር እድገቱ ከኢኮኖሚ እደገቱ ጋር የተጣጣመ ለማድረግ ያስችላል።

3.2.3. ሥነ-ሕዝብና የትምህርት ሁኔታ

የአንድ ሀገር ትልቁ ሀብት የሰው ሀይል በመሆኑ ለዘላቂ ልማትና ብልጽግናን ለማረጋገጥ ዋናው መሰረት የሰው ሀይል ነው። ስለሆነም ዜጐች ተገቢውን ዕውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት ጨብጠውና በመልካም ሥነ-ምግባር ታንፀው ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትን ተላብሰው ለራሳቸው፣ለማህበረሰባቸውና ለሀገራቸው ሊያበረክቱ የሚችሉትን አስተዋጽዖ በማጎልበት ለያዝነው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት መሰረት የሚሆኑ ዜጎችን ማፍራት ያስችላል።ነገር ግን ከፍተኛ ውልደትና ውጤቱ የሆነው ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በትምህርት አቅርቦትና ጥራት ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያስከትል ይታመናል። በክልሉ በአሁኑ ወቅት የሚታየው የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በመማር ዕድሜ የሚገኝ የሕዝብ ቁጥር በከፍተኛ መጠን እየጨመረ እንደሚገኝና ሁኔታውም የትምህርት ፍላጎትን ከተገቢው ደረጃ በላይ በማሳደግ በትምህርት አገልግሎት አቅርቦትና የጥራት ደረጃ እንዲሁም ለየደረጃው ብቁ የሆኑ መምህራን ሽፋን ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርጋል። በመሆኑም ሀገሪቱ የምትፈልገውን የተማረ የሰው ሀብትን ለማልማትና ኢኮኖሚውን ለመደገፍ ችግሩን በዘላቂነት

ለመፍታት ከባለድርሻ አካላትና ከህብረተሰቡ ጋር በቅንጅት በመስራት ተግባሩን መምራት ይገባል።

3.2.3.1. የትምህርት ፍትሐዊነትና ተደራሽነት

3.2.3.1.1 *የቅድመ አንደኛ ትምህርት*

ህፃናት ጥራት ያለውን የቀዳማይ ልጅነት ዘመን ትምህርትና እንክብካቤ ካገኙ ተፈጥሮ የለገሰቻቸውን ዕምቅ አቅማቸውን የማውጣት ዕድላቸውን የሚያሰፋና ዓለማችንን በተሻለ ደረጃ ማስቀጠል የሚችሉ ዜጎች መሆናቸው የማይካድ ሀቅ ነው። በመሆኑም የቅድመ አንደኛ ትምህርት በጥራት ህፃናት እንዲያገኙ ማድረግ ለህፃናቱ ብቻ ሳይሆን መላውን ሕብረተሰብ የሚለውጥ በመሆኑ ትኩረት እንዲያገኝ ተደርጓል። በተለይም ሀገራችን የጀመረችውን የብልጽግና ጉዞ ዳር ለማድረስ መተኪያ የሌለው ሀብቷ የሰው ኃይል በመሆኑ ይህን ኃይል በአግባቡ ማሳደግ፣ መኮትኮትና ማልማት ከተቻለ የበለፀገች ሀገር የመፍጠር ራዕይ ዳር መድረሱ አይቀሬ ይሆናል።

በመሆኑም በ2017 ዓ.ም የመማር ማስተማር ስራ እየሰሩ በሚገኙ 154 የቅድመ አንደኛ ትምህርት ቤቶች 124,989 ተማሪዎችን ለመመዝገብ ታቅዶ 101,300 (81%) መመዝገብ ተችሏል።አፈጻጸሙ ከ2017 ዓም እቅድ አንጻር ውጤታማ ቢሆንም ከአጠቃላይ ጥቅል ተሳትፎ አንጻር 35.6% ላይ የሚገኝ መሆኑ ሲታይ አፈጻጸሙ እጅግ አነስተኛ መሆኑን የሳያል። በመሆኑም የቅድመ አንደኛ ትምህርት ተሳትፎን ለማሳደግ የግንዛቤ ማስጨበጫ ውይይት በማድረግ የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ ለትምህርት የደረሱ ህጻናት ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዲመጡ በቅንጅት መስራት ይገባል ።

3.2.3.1.2 *የመጀመሪያ ደረጃ (1ኛ-6ኛ) ትምህርት*

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን ፍትሀዊ በሆነ መልኩ በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች ተደራሽ በማድረግ ሕፃናት ረዥም መንገድ እንዳይጓዙ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ተደራሽ ከማድረግ አኳያ በ1568 አንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አገልግሎት እየሰጡ ይገኛል። በ2017 ዓ.ም የአንደኛ ደረጃ (ከ1ኛ-6ኛ) ክፍል 584755 ተማሪዎችን ለመመዝገብ ታቅዶ 476589 (82%) ማከናወን ተችሏል። አፈጻጸሙ

ከ2017 ዓም እቅድ አንጻር ውጤታማ ቢሆንም ከአጠቃላይ ጥቅል ተሳትፎ አንጻር 62.8% ላይ የሚገኝ መሆኑ እንዲሁም የትምህርት ደረጃው ንጥር ተሳትፎ 55.9 መሆኑ ሲታይ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅልና ንጥር ተሳትፎን ለማሳደግ አሁንም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት መስራት የሚገባ መሆኑን ያመላክታል ።

3.2.3.1.3 *የመካከለኛ ደረጃ (7ኛ-8ኛ) ትምህርት*

የመካከለኛ ደረጃ (ከ7-8ኛ) ክፍል 115,484 ተማሪዎችን ለመመዝገብ ታቅዶ 83651 (72%) በመመዝገብ የመማር ማስተማር ተግባር ተከናውኗል። አፈጻጸሙ እቅድ አንጻር ውጤታማ ቢሆንም ከአጠቃላይ ጥቅል ተሳትፎ አንጻር 55.8% ላይ የሚገኝ መሆኑ እንዲሁም ንጥር ተሳትፎ 39.1% ላይ መሆኑ ሲታይ የትምህርት ደረጃው ጥቅልና ንጥር ተሳትፎን ለማሳደግ አሁንም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት መስራት የሚገባ መሆኑን ያመላክታል ።

በአጠቃላይ በክልሉ ካለዉ እድሜ ስብጥር አንጻር ወደ ትምህርት እድሜ ክልል የሚገቡ ህጻናት ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ የየትምህርት ደረጃውን ጥቅልና ንጥር ተሳትፎ ለማሳደግ ጥረቱ በስፋት መቀጠል እንዳለበት አመላካች ነው። *(ትምህርት ቢሮ 2017 ዓም ሪፖርት)*

3.2.3.1.4 *የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ-12ኛ) ትምህርት*

ሀገራችን በመካከለኛ ደረጃ ለሚያስፈልጋት የሰለጠነ የሰው ሀብት ልማት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መሠረት የሚጣልበት እና በተለይም ተማሪዎች 11ኛ እና 12ኛ ክፍል የሞያና የተግባር ትምህርቶችን ወስደው ስራ ፈጣሪ እንዲሆኑ ማስቻል እና ለከፍተኛ ትምህርት ለማዘጋጀት ወሳኝ ነው። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ወጣቶች አምራችና ጤናማ ኑሮን መኖር እንዲችሉ እንዲሁም በሀገራቸው ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጉዳዮች የነቃ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያዘጋጅ መሆኑን በርካታ ጥናቶች ይጠቁማሉ።

በክልላችን በመንግስትና በህብረተሰቡ በተደረገው ጥረት 184 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በመገንባት ለማህበረሰቡ ተደራሽ ማድረግ ተችሏል።

በዚህም በ2017 ዓም 120,576 ተማሪዎችን ለመመዝገብ ታቅዶ 87,332 (72%) ማከናወን የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ ከእቅድ አንጻር ውጤታማ ቢሆንም ከአጠቃላይ ጥቅል ተሳትፎ አንጻር 23.8% እንዲሁም ንጥር ተሳትፎ 18.2% ላይ መሆኑ አፈፃፀሙ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ተማሪዎች በትክክለኛው እድሜያቸው ወደ ትምህርት ቤት መሄዳቸው የህዝብ ቁጥር እድገትን ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ለማጣጣም በሚደረገው ጥረት ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ይህም የተማረ የሰው ሐይል ለስራ ገበያው በማቅረብ ፤የህዝብ እድገት በመቆጣጠር፤የገቢ መጠን በማሻሻል እና ድህነትን በመቀነስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

ስለሆነም በሁሉም የትምህርት ደረጃ ያለው ጥቅልና እና ንጥር ተሳትፎ ዝቅተኛ በመሆኑ በዘርፉ የሚሰራው ሥራ ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅና የክልሉን የተማረ የሰው ኃይል እድገት ለመጨመር መሰረት የሚጥል በመሆኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራት ይገባል፡፡

3.2.3.1.5 *የሴቶች ትምህርት ተሳትፎ*

የሴቶች ትምህርት ተሳትፎን ለማሳደግ በወንዶችና በሴቶች የተመዘገበ የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔን በማጥበብ የሴቶች ትምህርት ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ ከአድሎ ነፃና ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት ቤት አካባቢና ፋሲሊቲዎች መሟላት፣ በመምህራን መካከል የፆታ ምጥጥን እንዲኖር ማድረግ እና በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች እንዲካተቱ ማድረግ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

በዚህም መሰረት በ2017 ዓም የጾታ ምጥጥን በአንደኛ ደረጃ 0.88 ፣ በመካከለኛ ደረጃ 1፡1 እና በሁለተኛ ደረጃ 1፡12 ደርሷል፡፡ይህም ባለፉት አመታት ሴት ልጅን ከማስተማር አንጻር ሲደረጉ የነበሩ ጥረቶች ውጤታማ መሆናቸውን ያመላክታል፡፡ *(ትምህርት ቢሮ ሪፖርት 2017ዓ.ም)*

3.2.3.1.6 *የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት*

የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተሳትፎ በቅድመ መደበኛ ትምህርት አንጻር ፍላጎት ትምህርት ተሳትፎ አንጻር ለአካል ጉዳተኛ ሕፃናት ለቀጣይ አካላዊ እድገታቸው እና መሠረታዊ ክህሎት የሚይዙበት ስለሆነ ሁሉም እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ህፃናት ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ ለህብረተሰቡ ግንዛቤ በመፍጠር ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት ይጠይቃል። በመሆኑም በቀጣይ አምስት ዓመታት ከቅድመ አንደኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ባለው የትምህርት እርከን የልዩ ፍላጎት ያላቸውን ሕፃናት የመማር መብታቸውን በማክበር ሁሉም ባለድርሻ አካላት በትኩረት እንዲሰሩ ማስተባበር ይገባል።

3.2.8.የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጐልማሶች ትምህርት

የጐልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ዋና ትኩረት ጐልማሳው ከመሠረታዊ ትምህርት ባሻገር በሀገራችን ልማት እንቅስቃሴ ላይ ንቁና ወሳኝ ተሣትፎ እንዲያደርግ ከሕይወቱና ከሥራ ጋር የተሳሰረ ትምህርትና ሥልጠና በመስጠት ምርታማነቱን፣ ጤናውን፣ ኑሮውን እንዲሁም ማህበራዊ ተሳትፎውን ትርጉም ባለው ሁኔታ እንዲያሻሽል ማድረግ ነው። በዚህም ጎልማሳው የትምህርትን ጥቅም ተረድቶ ተገቢውን ዕውቀት፣ክህሎትና አስተሳሰብ እንዲይዝ በትምህርት ዘርፍ ተግባሩ ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ በመሆኑ መሰረታዊ የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ያለውን ፋይዳ በመረዳት ሁሉም ጎልማሳ በተለይ ሴቶች በአቅራቢያቸው አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ቤት በመክፈት ዕድሉን በማመቻቸት የዜጎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ርብርብ ያስፈልጋል። በመሆኑም በክልል ደረጃ በ2017 ዓም ወንድ 52,096 ሴት 41,504 ድምር 93,600 ጎልማሶችን ለመቀበል ታቅዶ ወንድ 31,981 ሴት 27,014 ድምር 58,895 (57.58%) ማሳካት ተችሏል። ይህም በመሠረታዊ የጎልማሶች ትምህርት መርሃ-ግብር ላይ የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል በቀጣይ ዓመታት ተጠናክሮ ሊሰራ እንደሚገባ ያመላክታል::

3.2.9 የትምህርት ጥራትና ተገቢነትን ከማረጋገጥ አንጻር

የትምህርት አመራሩ ትምህርት ቤቶች በብቃት በመምራት የሚፈለገዉን የሰዉ ሀይል ከማሟላት አንጻር በክልላችን የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን ተመርቀው በማስተማር ስራ ላይ የሚገኙ መምህራን ማብቃት ተገቢ ይሆናል። የክፍል-ተማሪ ጥምርታ ከ1-8 በ2017ዓ.ም 1፡41 ፤ከ9-12 የክፍል-ተማሪ 1፡45 ጥምርታ መሆኑን ያሳያል።

የተማሪ መጽሀፍ ጥምርታን በስታንዳርዱ መሰረት አሳትሞ ለተማሪዎች ለማቅረብ በተደረገው ጥረት የተማሪ መጽሀፍ ጥምርታን በሁሉም የክፍል ደረጃ 1፡1 ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙ በአማካይ በ2017 ዓ.ም ከ1-6ኛ ክፍል 1፡6 ፤መካከለኛ ደረጃ ከ7-8 ኛ ክፍል 1፡8 ፤የሁለተኛ ደረጃ ከ9-12 1፡1 ማድረስ ተችሏል።

የትምህርት ቤቶችን ደረጃ በተከታታይነት በማሻሻል ለመማር ማስተማር ሂደቱ ምቹ በማድረግ ጥራት ያለው ትምህርት ከመስጠት አንጻር ደረጃ 3 የደረሱ የአንደኛና የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ሽፋን በ2017 ዓም በቁጥር 86 ፤ደረጃ 3 የደረሱ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ሽፋን በቁጥር 16 መሆኑ በአጠቃላይ በሁሉም የትምህርት ደረጃ የት/ቤቶችን ደረጃ ከማሻሻል አንጻር በጣም በርካታ ስራ መስራት የሚጠይቅ መሆኑን ያሳያል። *(ትምህርት ቢሮ ሪፖርት 2017)*

3.2.9. ሥነ-ሕዝብና የከተማ ልማት ሁኔታ

በከተማ ያለው ህዝብ ቁጥር መጨመር የአገልግሎት አቅርቦት ላይ መዘግየት እንዲከሰት እና የከተማ ነዋሪው ላይ ተፅዕኖ እንዲደርስ ያደርጋል። በዚህም አብዛኛዎቹ ከተሞች ለኑሮና ለስራ ምቹ አለመሆን፣ጽዱና አረንጓዴ አለመሆን፤ዘመናዊ የከተማ ልማት አካሄድን አለመከተል፣ የተለያየ ማህበራዊ ችግሮችን የሚያስተናግዱና የስራ አጥ መከማቻ መሆን፣በቂ ኢኮኖሚ የማያመነጩ፣ ከፍተኛ የቤት እጥረትና የመሰረተ ልማት ችግር ያሉባቸው መሆን፣ የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ችግር፤በቂ የመዝናኛ ስፍራና የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት አለመኖር ተግዳሮቶች ያሉበት ነው።

በዚህም በ2017 በጀት ዓመት ከከተማ የሚመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ሽፋን 60%፤ፕላስቲክ ቆሻሻ መልሶ ጥቅም ማዋል ሽፋን 9.68% ፣ ከተሞቻችን ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገሩ እንዲሆኑ ለማስቻል በከተሞች የአረንጓዴ እጽዋት ልማት ሽፋንን 27% ፣ በከተማ ውስጥ በተራቆቱ ቦታ በተፋሰስና በመንገድ ዳር ግራና ቀኝ የጥላ የዛፍ ችግኝ እና የውበት ዛፍ ተከላ *13,683,284(91.2%)* ፣ በከተማ አረንጓዴ ልማት ላይ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ተደራጅተዉ ለ600 (ከ67.3%) ዜጎች ሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል።

የመኖርያ ቤት ጥያቄን በከተሞች ለመፍታት ማህበረሰቡን በህብረት ስራ ማህበራት በማደራጀትና የህብረተሰቡ የቤት ተጠቃሚነት እንዲያድግ ለማድረግ በከተሞች በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራት 601(75%) ቤቶች የተገነቡ መሆኑ ፤በአነስተኛ ገቢ ለሚተዳደሩ ሰዎች 43 (43%) ወጪ ቆጣቢ ቤቶች፤ እንዲሁም የደሃ ደሃ ቤት አቅርቦትን በማሳደግ በድህነት እና በቤት ዕጦት ላሉ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ቅድሚያ እንዲያገኙ ከማድረግ አንጻር 251 ቤቶች መገንባት ተችሏል።

እንደአጠቃላይ ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴ እንዳለ የሚያሳይ ቢሆንም በከተሞች ስር ሰዶ የቆየውን ድኅነትና ኋላቀርነትን ለመቀነስ የነዋሪውን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን በተሻለ ሁኔታ በመፈጸም በከተሞች የስነ-ህዝብና ተያያዥ ችግሮችን ለመፍታት የተለየ ትኩረት በመስጠት መስራት ያስፈልጋል። *(ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ብሮ 2017 ሪፖርት)*

3.2.10. ሥነ-ሕዝብና ንጹህ መጠጥ ውሃ ሁኔታ ትንተና

በክልሉ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ካለው የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር በተጓዳኝ አብሮ ሊያድግ ከሚገባቸው የተለያዩ መሰረታዊ ፍላጎቶች ዋናው የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋንን ማሳደግ ነው። የነበረውንና በየዓመቱ የሚጨምረውን የሕዝብ ቁጥር ታሳቢ ያደረገ ንጹህ የመጠጥ ውኃ አገልግሎት ተደራሽ የማድረጉ ሥራ ከየትኛውም ተግባር በላይ ቀዳሚውና ዋነኛው ጉዳይ ነው። አብዛኛዉ የክልሉ አከባቢዎች በከተማም ሆነ በገጠር የንፁህ መጠት ዉሃ ተደራሽ ከማድረግ አንጻር ገና የሚቀርና ተደራሽ ያልተደረገ

በመሆኑ በተለይ በገጠር የሚኖረው የህብረተሰብ ክፍሎች በተለያዩ ፕሮጅክቶች ንጹህ የመጠጥ ዉሃ ለማግኘት ክልሉ እየሠራ ቢሆንም አሁንም አንድንድ አከባቢዎች ለንጹህ መጠጥ ዉሃ ረጅም ርቀት እየተጓዙ ይገኛሉ፡፡ በዚህ መሰረት በ2017 ዓ.ም መጨረሻ በገጠር፤ በ1 ኪ/ሜ ርቀት በቀን 25 ሊትር ውሃ እያገኙ ያሉት 40.78% ፣በከተማ 60% መሆኑና በአማካይ ክልላዊ የዉሃ ሽፋን 43.83% (ከግማሽ በታች) መፈጸም ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ በክልሉ የንፁህ መጠጥ ዉሃ ሽፋን ካለፈዉ 2016 ዓ.ም በጀት ዓመት በገጠርና ከተማ ያለዉን የንጹሕ መጠጥ ውሀ አቅርቦት ሽፋን አማካይ ከ42.8% ወደ 43.83% ወይም 1.03% ብቻ ለዉጥ ማሳየቱ ሽፋኑ በጣም አዝጋሚና በቀጣይ አምስት ዓመታት የክልሉን ንጽህ መጠጥ ዉሃ ሽፋን በሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች ለማዳረስ የባለድርሻ አካላት መንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በንፁህ መጠጥ ዉሃ ግንባታ ላይ ርብርብ እንዲያደርጉ ትኩረት ሰጥቶ መሠራት እንዳለበት የአፈጻጸሙ ውስንነት አመላካች ነው፡፡ *(ዉሃና ማዕዲን ቢሮ ሪፖርት 2017)*

3.2.11 *ሰነ-ህዝብና የሥራ አጥነት ሁኔታ*

ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ያልተጣጣመ የህዝብ ቁጥር እደገት መኖር ከሚያስከትለው ማህበራዊ ችግሮች አንዱ ስራ አጥነት ነው፡፡ስራ አጡ የህብረተሰብ ክፍል የሥራ ዕድሎችን ያላገኘ መሆኑ ፤ ስራን ፈጥሮ የመስራት ባሕሉ ባለመዳበሩ ምክንያት የመንግስት ስራ ብቻ በመጠበቅ ለከፋ ሥራ አጥነት እየተዳረገ ነው፡፡ ሥራ አጥነቱ በከተሞች አካባቢ እየተባባሰ ሲሄድ ሌብነት፣ ዝርፊያ፣ የፖለቲካ አለመረጋጋትና የተለያዩ የወንጀል ዓይነቶች በመበራከታቸው በማህበረሰቡ ላይ አለመረጋጋትን እየፈጠረ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ለሥራ ፈላጊዎች ከመንግስት የብድር አገልግሎትና የተለያዩ የሥራ ዕድሎችን ማመቻቸት እንዲሁም የመስሪያ ቦታዎችን ሆነ ሌሎች አማራጮች የሚመቻችበት ሁኔታ ትኩረት ቢሰጠው ችግሩን በመጠኑም ቢሆን መቀነስ ይቻላል፡፡

በዚህም በ2017 ዓ.ም በክልሉ ለዜጎች የስራ እድል ከመፍጠር አንጻር በሀገር ዉስጥ የስራ ስምሪት ድጋፍ ለ52,388 የገጠርና ከተማ ሥራ ፈላጊ ዜጎች በግብርና

ዘርፍ፣በኢንዱስትሪ ዘርፍና በአገልግሎት ዘርፍ በቋሚነት ድጋፍ በመስጠት ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ተደርጓል። በጊዜያዊ የሥራ ዕድል ለ88,656 ሥራ ፈላጊዎች የስራ ዕድል እንዲያገኙ በማድረግ በተጨማሪ የልማት ድርጅቶች የሰራተኛ ፍላጎትን ወቅታዊ ምላሽ በመስጠት እና የልማት ድርጅቶችን የሠራተኛ አቅርቦትን በማሳለጥ የልማት ግባቸዉን እንዲያሳኩ ድጋፍ ተደርጓል። *(ሥራና ክህሎት ቢሮ ሪፖርት2017)*

ይሁን እንጂ በክልሉ ከሚታየው የሥራ ፈላጊ ቁጥር አንፃር ወደ ስራ የተሰማራው በሚፈለገው ደረጃ ላይ አይገኝም። ስለሆነም ዜጎች ስራ ፈጣሪ እንዲሆኑ የሚያስችል ክህሎት፣እዉቀትና ልምድ እንዲኖራቸዉ በቂ የሆነ ትምህርትና ስልጠና መስጠት፣በቂ የሰው ኃይል መቅጠር የሚችሉ የልማት ድርጅቶች ቁጥር በሚፈለገው ደረጃ በማሳደግ፣ ለስራ ፈላጊ ዜጎች የስራ እድል በመፍጠር የስራ አጥነት ምጣኔ እንዲቀንስ ተገቢዉን ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል።

3.2.12 ሥነ-ህዝብና ማህበራዊ ሁኔታ

በሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ማህበራዊ ደህንነት እና ጥበቃ ለሀገሪቱ የሰው ሀይል ልማትና ማህበራዊ መረጋጋት እጅግ ወሳኝ ምሰሶ ነው። በተለይም ፈጣን የህዝብ ቁጥር እድገት በሚታይበት አውድ ውስጥ፣ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን መደገፍና አቅም መፍጠር የዘላቂ ልማት መሰረት ነው ይህ ዘርፍ የህብረተሰቡን መሰረታዊ የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻልና ማህበራዊ መስተጋብርን ለማጠናከር የሚደረጉ አጠቃላይ ድጋፎችን ያጠቃልላል።

3.2.12.1 ሥነ-ህዝብና ሥርዓተ-ጾታ

ሴቶች በህብረተሰቡ ውስጥ በማንኛውም መስክ ሰብአዊ፣ የንብረት ባለቤትነትና ተቆጣጣሪነት መብታቸው እንዲከበርና እኩልነታቸው እንዲረጋገጥ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊና በፖለቲካ እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚሆኑበትን የተመቻቸ ሁኔታ እንዲፈጠር ለዘመናት ሥር ሰዶ የቆየውን በየታ ላይ የተመሠረተ ልማዳዊና አድሎአዊ አስተሳሰብ ደረጃ በደረጃ ለማጥፋትና ሴቶች በውሳኔ ሰጪነት ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ

መንግሥታዊ ስልጣንና አስተዳደር ውስጥ እኩል ተሳታፊ እንዲሆኑ ሴቶች በራሳቸው በጋራ ተደራጅተው እንዲታገሉ ግንዛቤያቸውን ማሳደግ ይጠይቃል፡፡

በዚህም በ2017 ዓ.ም የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ከማሳደግ አንጻር መብቶቻቸውን ለማስጠበቅ የሚረዱ ተግባራት ላይ ትኩረት በመስጠት የቁጠባ ባህላቸውን በማሳደግ 114,941,927 እንዲቆጥቡ በማድረግ **93,647 ሴቶች በተለያዩ የገቢ** ማስገኛ ስራዎች ማሰማራት ተችሏል፡፡የሴቶች በአመራርና ውሳኔ ሰጭነት ተሳትፎን ከማሳደግ አንጻር ለአመራር ፑል ብቁ የሆኑ 28,321 ሴቶች ፤ አመራር ፑል ከተካተቱ ውስጥ ወደ አመራር የመጡ ሴቶች ድርሻ 46 ማካተት ተችሏል፤ የአስፈጻሚ የሴቶች ድርሻ ከጠቅላላ አመራር 15.41%(412) ማደረስ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በሴቶች ላይ የሚደርስ የሥራ ጫና የሚቀንሱ ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ተደራሽ ከማድረግ አንጻር በ2017 ዓ.ም 60,347 ሴቶችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ *(ሴቶችና ማህበራዊ ቢሮ ሪፖርት 2017)*

በአጠቃላይ የሴቶችን ተጠቃሚነትና ተሳታፊነትን በሚፈለገዉ ልክ ለማረጋገጥ በሴቶች ላይ የሚደርሱ የሥራ ጫና የሚቀንሱ ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ የሆኑ ተክኖሎጅዎችን ተደራሽ በማድረግና የማህበረሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ ሴቶች አብዛኛውን ጊዜያቸውን ልጅ በመውለድና በማሳደግ፣ ምግብ በማዘጋጀት፣ ለማገዶ የሚሆን እንጨት በመሰብሰብ እና ውሃ በመቅዳት የሚያባክኑትን ጊዜ በማሳጠር በትምህርትና የውሳኔ ሰጪነት ሚናቸውን እንዲሁም ኢኮኖሚያቸውን እንዲያሳድጉ ለማድረግ አሁንም ከፍተኛ ጥረት ማድረግን ይጠይቃል ::

3.2.12.2 *ሥነ ህዝብና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች*

በክልሉ በሴቶችና በህጻናት ላይ የሚፈጸሙ በርካታ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አሉ ተብሎ ይገመታል፡፡ በክልሉ ውስጥ ጎልተው ከሚታዩት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ውስጥ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ ጠለፋ፣ አስገድዶ መደፈር፣ ድርብ ጋብቻና የሴት ልጅ ግርዛት ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡አብዛኛውን ጊዜ የጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ተጠቂ የሆኑ ሴቶች እና ህጻናት ለማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ሥነ-ልቦናዊ ጫና ተጋላጭነታቸው ከፍተኛ ነው፡፡

በመሆኑም በክልሉ በ2017 ዓም ከጎጂ ልማዳዊ ድርግቶች ነፃ የሆኑ ቀበሌያት ሽፋን ከማሳደግ አንጻር 64 ቀበሌያት ከጎጂ ልማዳዊ ድርግቶች ነፃ የወጡ ሲሆን በአጠቃላይ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ለሀገራዊ የልማት እንቅስቃሴና ዕድገት እንቅፋት በመሆናቸው ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ግንዛቤ በመፍጠር በቀጣይ ጊዜያት የሴቶችንና የህጻናቱን ደህንነት በማረጋገጥ ለሀገራዊ እድገት ሊያበረክቱ የሚችሉትን ዕድል ከፍ ለማድረግ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ብዙ ሥራ መሰራት እንዳለበት አመላካች ነው።

3.2.12.3 *የአካል ጉዳተኞች ሁኔታ*

የአካል ጉዳተኝነት በሀገራችንም ሆነ በክልሉ ተገቢውን ትኩረት ያላገኘ የማህበራዊ ኑሮ ችግር ሲሆን አካል ጉዳተኞች በሁሉም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተገቢውን ተሳትፎ በማድረግ ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ የሚመለከታቸውን አካላት በመምራትና በማስተባበር የአካላዊ እና የማህበራዊ የተሃድሶ አገልግሎቶች እንዲያገኙ ይደረጋል።

በዚህ መሰረት ከረጂ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በ2017 ዓ.ም በክልሉ ከድህነት ወለል በታች የሆኑ በመሰረታዊ ማህበራዊ አገልግሎት በተሃድሶ ማዕከል የተቀናጀ አገልግሎት ተጠቃሚ ዜጎች 5,140፣408 አካል ጉዳተኞች የሰው ሰራሽ አካል፣የአካል ድጋፍ እና የማህበራዊ ተሃድሶ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል። ከዚህ በተጨማሪም በክልሉ አንድ አካል ጉዳተኞች የህክምናና ተሃድሶ ማዕከል ግንባታ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል። (ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ሪፖርት 2017)

በአጠቃላይ አካል ጉዳተኞች አቅማቸውንና ችሎታቸውን በመጠቀም አምራችና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበርና በመቀናጀት የትምህርት እና ስልጠና እድሎች እንዲመቻቹላቸው እና በማንኛውም የስራ መስክ እንዲሰማሩ በማድረግ በክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የራሳቸዉን አስተዋጽኦ የሚያበረክቱበት አግባብ መጠናከር አለበት።

3.2.12.4 *የፍልሰት ሁኔታ*

ፍልሰት የስራ ፍለጋ፣ ትምህርት፣በአጠቃላይ የተሻለ ኑሮ ለመኖር ከመንደር ወደ ከተማ ፣ከአንድ ክልል ወደ ሌላ ክልል ወይም ከአንድ ሀገር ወደ ሌላ ሀገር የሚደረግ እንቅስቃሴ ቢሆንም በሀገርና በማህበረሰብ ላይ የተለያዩ ተጽእኖዎችን ያሳድራል፡፡በዚህም በ2017 ዓ.ም ለ90733 ዜጎች ህገ-ወጥ ፍልስት ላይ ያተኮረ የአቻ ለአቻ እና የህይወት ክህሎት ውይይት በማድረግ ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ተጋላጭነትን ለመቀነስ የሚያስችል ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ተሰርቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከፍልሰት ለተመለሱ 473 ዜጎች የስነ-ልቦና፣ የማህበራዊ እና ሌሎች አገልግሎቶችን ድጋፍ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ችግሩ ጎልቶ በሚታይባቸው ዞኖች መደበኛ ያልሆነ ፍልሰት ተመላሽ ዜጎችን ለመደገፍና መልሶ ለማቋቋም በገንዘብና በአይነት ሀብት 231,118 ብር በማሰባሰብበ መደገፍ ተችሏል ፡፡ (ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ሪፖርት 2017)

በአጠቃላይ በቀጣይ አምስት ዓመት ውስጥ በየአካባቢው ችግሩ እየታየባቸው በሚገኙ ዞኖች ላይ የተለያዩ የሥራ ዕድሎችን ለወጣቱ ማመቻቸት ለምሳሌ የብድርና ቁጠባ ስርዓት፣የመስሪያ ቦታ ማመቻቸት፣የተለያዩ የሙያ ስልጠናዎችን በመስጠት እና በየአካባቢ ለኑሮ ምቹ ሁኔታዎች በመፍጠር ፍልሰትን ማስቆም አለያም እንዲቀንስ ማድረግ ይገባል፡፡

3.2.12.5 *የጎዳና ተዳዳሪነት ሁኔታ*

ጎዳና ተዳዳሪነት የማህበራዊ ኑሮ ጠንቅ እንደመሆኑ መጠን የመላው ህብረተሰብ ወግና አኗኗር የማናጋትና ገጽታ የማበላሸት አስተዋጽኦ አለው፡፡ ለጎዳና ተዳዳሪነት መስፋፋት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ይዘት ያላቸው በርካታ ምክንያች ቢኖሩም ኤች/አይ.ቪ/ኤድስን ጨምሮ በተለያዩ ምክንያቶች ወላጅን ማጣት፣ የጋብቻ መፍረስ፣ ድህነት፣ ያልተመጠነ የቤተሰብ ቁጥር መኖርና የሥራ ፈጠራ ባህል አለመዳበር ከሚጠቀሱት ምክንያቶች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ በ2017 በጀት አመት 310 በተለያዩ ምክንያት ወደ ጎዳና ለወጡ ዜጎች የተለያዩ አገልግሎቶችን እንዲያገኙና ከቤተሰቦቻቸዉ እንዲቀላቀሉ የተለያዩ ድጋፎች ተደርገዋል፡፡

የጎዳናው ኑሮ ወንዶችንና ሴቶችን እኩል የሚያስተናግድ ቢሆንም ከወንዶች ይልቅ ሕይወት ለሴቶች ቀላል አይሆንም እነዚህ ሴቶች ከፍላጎታቸው ውጪ በሚደርስባቸው የአስገድዶ መደፈር ምክንያት ላልተፈለገ እርግዝና፣ ለኤችአይቪ/ኤድስና ለሌሎች ተላላፊ በሽታዎች ስለሚጋለጡ ለቀውሱ መባባስ የሚያበረክቱት አስተዋጾ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች የተለያዩ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ በማህበራዊ ልማት ተሳታፊ በማድረግ በገቢ ማስገኛ ሥራዎች በማሳተፍ ራሳቸውን ከማቋቋም አልፈው በህብረተሰቡ ሰላምና ጸጥታ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት በመቀነስ ረገድ ሚናው ከፍተኛ ስለሆነ በቀጣይ የባለድርሻ አካላትን ርብርብ ይጠይቃል፡፡

3.2.13. ሥነ-ሕዝብና የሥነ-ተዋልዶ ጤና ሁኔታ

3.2.13.1. *የሥነ-ተዋልዶ ጤና*

የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ጤናማና በፍላጎት ላይ የተመሠረተ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም፣በራስ ውሳኔና ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የመውለድም ሆነ ያለመውለድን የመወሰን፣አቅርቡቱ የተመቻቸና የመግዛት አቅምን ያገናዘበ የጥራት ደረጃውን የጠበቀና ተቀባይነት ያለው የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት የማግኘት፣ እርግዝናና በወሊድ ወቅት ጥራቱን የጠበቀ የሕክምና አገልግሎት የማግኘትና ጤናማ ልጅ የመውለድ የልጆችን መጠንና የሚወልዱበት የጊዜ ርቀት የመወሰን፤ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ጨምሮ በግብረ ሥጋ ግንኙነት አማካይነት የሚተላለፉ በሽታዎችን የመከላከልና የማከም እንዲሁም የተሟላ ወቅታዊ የሆኑ የቤተሰብ ምጣኔ መረጃዎችንና የምክር አገልግሎቶችን የማግኘት መብቶችን ሁሉ የሚያጠቃልል ነዉ፡፡

በአጠቃላይ ተዋልዶ ጤና ሁሉንም ተዋልዶአዊና ወሲባዊ ጤንነቶችን መንከባከብን በዚህም ዘርፍ ተገቢውን መረጃና አገልግሎቶችን ማዳረስ እንዲሁም ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ማስወገድን የሚይዝ ሰፊ የጤና ዘርፍ ሲሆን ችግሩ ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል የሚያጠቃ ቢሆንም በተለይም እናቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች የችግሩ ግንባር ቀደም ተጠቂዎች ናቸው፡፡

የክልሉ ሕዝብ እያደገ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አሁን ባለው 3,956,358 የክልላችን ህዝብ ላይ በየዓመቱ ከ119,157 ሺህ በላይ ለሚደመረው ተጨማሪ ሕዝብ ታሳቢ ያደረገ እንደ ሪፈራል ሆስፒታል፣ ጤና ጣቢያና የመሳሰሉ የጤና ተቋማት እንዲሁም የጤና ባለሙያዎችና በቂ የህክምና መሳሪያዎች በተገቢው በማቅረብ ለህብረተሰቡ ጤና ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል፡፡

የጤና ተቋማትና አገልግሎትን በተመለከተ አዳዲስ ተቋማትን ጨምሮ በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል 12 አጠቃላይ ሆስፒታል 4 የግል ሆስፒታል 4 እንዲሁም 129 ጤና ጣቢያዎች 807 ጤና ኬላዎችና 462 የግል ክሊኒኮች 4 የግል ጤና ጣቢያዎች ለህብረተሰቡ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም ክልሉ ካለዉ የህዝብ ብዛት አንጻር ያሉት የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ብዛት በቂ ቢሆንም የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ክፍተት ያለባቸዉ በመሆኑ ከመንግስት በተጨማሪ የግሉን ዘርፍ ኢንቨስትመንት እና ተሳትፎ ማሳደግ ይጠይቃል፡፡ *(ምንጭ፡- 2017 ዓ.ም የጤና ቢሮ መረጃ)*

በዓለም ጤና ድርጅት ስታንዳርድ አንድ ዶክተር ከሚያገለግለው ህዝብ ጋር ያለው ጥምርታ 1፡10,000 ሲሆን የ2017 ዓ.ም በክልሉ ጤና ቢሮ መረጃ መሠረት የዶክተሮች ብዛት 168 ሲሆን አንድ ዶክተር (ሐኪም) በአማካይ ለ23,549 ሰዎች የህክምና አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ከዓለም አቀፍ ስታንዳርድ አንፃር ሲታይ በክልላችን የዶክተሮች ብዛት በጣም አነስተኛ መሆኑን ያሳያል ይህም በእናቶችና ህጻናት ጤና እንዲሁም በአጠቃላይ በህክምና አገልግሎት ላይ ከፍተኛ ጫና የሚያሳድር በመሆኑ በቀጣይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራበት ይገባል፡፡

በዓለም ጤና ድርጅት ስታንዳርድ አንድ ጤና መኮንን 10,000 ህዝብ የሚያገለግል ስሆን በክልሉ ያሉ የጤና መኮንን ብዛት 432 ሲሆን በአማካይ አንድ የጤና መኮንን ለ9,158 ህዝብ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል የዓለም ጤና ድርጅት ስታንዳርድ መሰረት አንድ ነርስ 5,000 ህዝብ የሚያገለግል ሲሆን በክልሉ ያሉ የነርስ ድግሪና ድፕሎማን ጨምሮ 2,086 ስሆኑ አንድ ነርስ በአመካይ ለ1,896 ህዝብ ያገለግላል ማለት ነዉ፡፡ የጤናውን ሴክተር ከብዛትና ጥራት አኳያ ያለውን ስታንዳርድ

አሚልቶ ለህብረተሰቡ የሚፈለገውን አገልግሎት ለመስጠት የሰለጠኑ ብቃት ያላቸው የጤና ባለሙያዎች ማሟላት ብቻ በቂ ስለማይሆን የመሠረተ ልማት ጉዳዮችን እና የህክምና ግብአቶችን የማሟላት ጉዳይ ዋና ዋና ትኩረት ከሚያስፈልጋቸው ውስጥ የሚመደብ መሆን አለበት፡፡ በመሆኑም በቀጣይ አምስት ዓመት ውስጥ የክልሉ ጤና ሴክተር ከባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ሥራ መሥራት እንደሚያስፈልግ አመላካች ነው፡፡ *(ፕላንና ልማት ቢሮ መረጃ 2017)*

3.2.13.2. *የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት*

የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት አንዱና ዋነኛው ለተዋልዶ ጤና ኘሮግራሞች እንደ ምሰሶ (pillar) ሆኖ ያገለግላል፡፡ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ችግርን ለመቅረፍ ከማገዙም በላይ በብዙ መንገዶች ለሀገራዊ ልማት አስተዋጽኦ አለው፡፡ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት አንድ ቤተሰብ የሚፈልገውን ልጅ መጠን ፈልጐና አቅዶ እንዲወልዱ የሚያስችል፣የተለያዩ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ዘዴዎችን እንዲመርጡ የሚረዳ፣ በአይነትና በጥራት አገልግሎቶችን የማቅረብ ሂደቶችን በሙሉ ያጠቃልላል፡፡ በመሆኑም የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚነትን በመጨመር በዋናነት የእናቶችንና ህጻናትን ህመምና ሞት መጠን መቀነስ ይቻላል፡፡በአጠቃላይ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎትን ማስፋፋትና ማጠናከር በክልሉ ካለው የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ጋር የተመጣጠነ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት እንዲኖር ከማስቻሉም በላይ የዜጎች ተዋልዶ ጤና ደህንነት ሁኔታ እንዲሻሻል ከፍተኛ ሚና አለው፡፡

የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎትን ከሚያስፈልጉ አማራጭ የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴ ግብአቶች ጋር ተጠቃሚዎች በሚመርጡትና በሚወስኑት ዓይነት፤ ቦታና ጊዜ ተደራሽ ማድረግ የተጠቃሚዎችን ቁጥር ይጨምራል፡፡ ይህንን ተከትሎ በ2017 የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎትን ሽፋን 78% መሆኑን የክልሉ ጤና ቢሮ ዕቅድ አፈጻጸም ይገልጻል፡፡

በሀገር ደረጃ በ1985 ዓ.ም ብሔራዊ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ ሲጸድቅ የአንዲት እናት አማካይ የውልደት ምጣኔ 7 ልጅ ትወልድ የነበረ ሲሆን በየክልሉ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተደራሽነትን ለማስፋፋት በተደረገው ጥረት የውልደት ምጣኔው እየቀነሰ

በመምጣቱ በ2016 ዓ.ም በክልሉ የአንዲት እናት አማካይ የውልደት ምጣኔ በገጠር 4 በከተማ 3 ልጆች ቁጥር ዝቅ ማድረግ ተችሏል። ይህም ለውጥ ሊገኝ የቻለው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላት የሕብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ፣ የጤና ተቋማትን አገልግሎት ለማስፋፋት፣ የባለሙያን ክህሎት ለመጨመር፣የግብአት አቅርቦትን ለማሻሻል በተቀናጀ ሁኔታ በመስራታቸው እንደሆነ ይታወቃል።

በክልሉ ያለውን የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ሽፋን በማሳደግ ህብረተሰቡ አገልግሎቱን በአግባቡ እንዲያገኝ በትምህርት ቤቶች በሥነ-ሕዝብ ክበብ አባላት በቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ዙሪያ ስልጠናዎችን በመስጠት ግንዛቤአቸውን ማዳበር፣ ሥነ-ሕዝብና ተዋልዶን በሚመለከት የሬዲዮና ቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ ተደራሽ በማድረግ፣ እንዲሁም የማህበረሰብ ማቀጣጠያ ውይይት እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲወያዩ በማድረግ፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሴክተሮችንና በጎአድራጎት ድርጅቶችን በማስተባበር፣ለተሳሳቱ ግንዛቤዎች ትክክለኛ መረጃ በመስጠት እንዲሁም በከተማና በገጠር ባሉ ጤና ተቋማት ሁሉንም ዓይነት አማራጭ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎቶችን በማቅረብ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎችን ቁጥር ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል።

3.2.13.3. *የእናቶች ጤና*

የእናቶች ጤና አገልግሎት ማለት በመውለድ የዕድሜ ክልል /ከ15-49/ ውስጥ ያሉትን ሴቶች የሚሸፍን እና ለሴቶቹ የሚሰጥ የቅድመ ወሊድና የድህረ ወሊድ ክትባትና ሌሎች አገልግሎቶችን የሚያጠቃልል ነው። በዚህም መሰረት የእናቶች ጤና አገልግሎት ሽፋንና ጥራትን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ ታቅዶ በ2017 ዓ.ም ቢያንስ 4 ጊዜ የቅድመ-ወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች ሽፋን ለ101,744 አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ86,482(85%)ማድረስ ተችሏል። እንዲሁም የድህረ-ወሊድ አገልግሎት ሽፋን በ2017 ዓ.ም ለ101,744 ለማድረስ ታቅዶ ለ86,482(85%) ማድረስ የተቻለ ሲሆን የተቻለ ሲሆን በሰለጠነ የጤና ባለሙያ የወለዱ እናቶች መጠን በ2017 በጀት ዓመት 96,172 ለመስጠት ታቅዶ ለ64,435(67%) መፈጸም ተችሏል። በሌላ በኩል ነፍሰ ጡር እናቶች

ለኤች/አይ/ቪ ኤድስ ምርመራ አገልግሎት ሽፋን በ2017 ዓ.ም ለ98,144 እናቶች ምርመራ ለመስጠት ታቅዶ ለ91,492(93%) ነፍሰ-ጡር እናቶች እንዲያገኙ ተደርጓል። ሲሆን ለእናቶች ሞት መጠን መቀነስ እና የኤች አይ ቪ ኤድስ ስርጭት ለመቀነስና የሥርጭት ምጣኔን ከመቀነስ አንጻር በተደረገዉ አጠቃላይ ምርመራ ዉስጥ 0.53% በኤች አይ ቪ የተያዙ መሆናቸዉ ተረጋጧል። *(ጤና ቢሮ ሪፖርት 2017)*

3.2.13.4. *የሕጻናት ጤና*

የሕፃናትን በሽታ እና ሞት ለመከላከል በስፋት ከሚተገበሩ አገልግሎቶች የክትባት መርሃ-ግብር አንዱ ሲሆን ባለፉት በ2017 ዓ.ም ሁሉንም ክትባት ጨርሰው የወሰዱ ሕጻናት ሽፋን 101,368 ለማድረስ ታቅዶ 98,228 የዕቅዱ 89% ማድረስ ተችሏል።በመሆኑም ከአንድ አመት በታች ህጻናት ሞት ምጣኔ 47/1,000፣ከአምስት አመት በታች ህጻናት ሞት ምጣኔ 76/ከ1,000 ሲሆን በክልሉ የሚወለዱ የህፃናትን ጤና በመጠበቅ የሞት ምጣኔን መቀነስ የተቻለ ቢሆንም በቀጣይ አምስት አመት ውስጥ የሚመለከታቸው ባለድረሻ አካላት በልዩ ትኩረት በመስጠት በመረባረብ የህጻናትን ሞት በእጅጉ መቀነስ ያስፈልጋል። *(ጤና ቢሮ ሪፖርት 2017)*

3.2.13.5. *ወጣቶችና ሥነ-ተዋልዶ ጤና*

ወጣትነት ከልጅነት የዕድሜ ክልል ወደ አዋቂነት የሚሸጋገሩበት ወቅትና ፈጣን አካላዊና አዕምሮአዊ ለውጦች የሚስተዋሉበትና የሚታዩ"በት የዕድሜ ክልል ነው። በመሆኑም ስለወሲባዊ ግንኙነትና የተዋልዶ ጤና ጉዳይ በቂ መረጃና የግንዛቤ እጥረት ያላቸው ብዙውን ጊዜ ወሲብ የሚፈጽሙት ጥንቃቄና ሀላፊነት በጎደለው ሁኔታ በመሆኑ በተዋልዶ ጤና ዙሪያ ብዙ ያልታሰቡ ችግሮች እያጋጠማቸው ይገኛል። ስለሆነም ለወጣቶች የሥነ ተዋልዶ ጤና ችግሮች መባባስ ምክንያት ከሆኑት ጉዳዮች ውስጥ መረጃ የሚያገኙባቸው ማዕከላት ያለመስፋፋት፣የመዝናኛና የጊዜ ማሳለፊያ ሥፍራዎች በበቂ ሁኔታ ያለመኖርና በሥነ ተዋልዶ ጤና ዙሪያ ወጣቶችን የሚያሳትፍ ፕሮግራሞች ውስንነት የሚጠቀሱ ናቸው።

በክልላችን 97 የወጣቶች ማዕከላት የተገነቡ ቢሆንም በሁሉም ወረዳዎችና ቀበሌዎች ተደራሽ ማድረግ ካለመቻሉም በተጨማሪ ማዕከላቱ ደረጃቸውን የጠበቁ ሳቢና ለአካል

ጉዳተኞች እና ሴት ወጣቶች ምቹና ተስማሚ አለመሆናቸው አንዲሁም አንዳንድ ማዕከላት ከተቋቋሙለት ዓላማ ውጪ ለሌላ አገልግሎት የሚውሉበት ሁኔታ መኖሩ እና በአጠቃላይ በስታንደርዱ መሰረት ያለመመራቱ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው፡፡

ወጣቶች በአስከፊ ድህነት፣በሥራ አጥነት፣የሥነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎት አለማግኘት ጋር ተያይዞ ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ይጋለጣሉ፤ ለአብነት ያለዕድሜ ጋብቻ፣ ላልተፈለገ እርግዝና፣ ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስና ሌሎች ተላላፊ በሽታዎች ተጋላጭ ይሆናሉ፡፡

ለኤች አይ ቪ/ኤድስና ለሌሎች ተላላፊ በሽታዎች የተያዙ ወጣቶች ለማህበራዊ፣ ለኢኮኖሚያዊና ለስነ ልቦና ችግሮች ሲጋለጡ ይስተዋላል፡፡ ስለሆነም መንግስትና በጤናው ዘርፍ የተሰማሩ ባለድረሻ አካላት ይህንን ጉዳይ በሚገባ ትኩረት በመስጠት የነገ ሀገር ተረካቢ ወጣቶችን ጤና ለማስጠበቅና በበሽታው የመጋለጣቸውን መጠን ለመቀነስ የወጣቶች ስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማትን በማስፋፋት፣ የወጣቶች መዝናኛ ማዕከላትን በመገንባት ለአገልግሎቱ ምቹ በማድረግ እንዲሁም በጤና ተቋማት ውስጥ ለወጣቶች ምቹ አገልግሎት መስጫ ቦታዎችን በማመቻቸት በቀጣይ አምስት ዓመት ውስጥ በትኩረት መስራትን ይጠይቃል፡

ክፍል አራት

4.1. ጥንካሬ፣ድክመት፣መልካም አጋጣሚዎችና ሥጋቶች (SWOT) Analysis

4.1.1. ጠንካራ ጎን

- የሴቶች ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ መምጣቱ
- በሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች የማህበረሰብ ንቅናቄ ውይይት እስከ ቀበሌ ድረስ ለማደርግ ምቹ የመዋቅራዊ አደረጃጀት፡፡
- በጤና ተቋማት የሚወልዱ እናቶች መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍ ማለቱና የሞት መጠን እየቀነሰ መምጣቱ፤
- የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ሽፋን ከፍ ማለቱ፤
- የግብርና ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር በርካታ ጥረት መደረጉ፤
- ለትምህርት ተደራሽነት በሚደረገው ጥረት የህብረተሰቡ ተሳትፎ አበረታች መሆኑ፤
- የአረንጓዴ አሻራ የማስቀመጥ ሥራ ሀገራዊ ትኩረት የተሰጠው መሆኑ፤
- በሁሉም መለስተኛ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሥነ-ህዝብ ክበባት የተቋቋመ በመሆኑ አበረታች ተግባራት እየፈጸሙ መሆኑ፤
- ማህበረሰቡ አማራጭ የኃይል ምንጮችን የመጠቀም ልምዱ እያደገ መምጣቱ፡፡

4.1.2. ደካማ ጎኖች

- የሥነ-ሕዝብ ም/ቤት በአብዛኛዉ ዞኖች፣ ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ማቋቋምና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ያለመቻሉ፡
- አመራሩ ለሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች የተፈለገውን ያህል ትኩረት ያለመስጠትና ወቅታዊ ግምገማ አለማካሄድ፤

- ቅንጅታዊ አሰራር እና የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል ያለማድረግ፤
- በሴቶች መብት አከባበርና እኩልነት ማረጋገጥ ላይ የግንዛቤ ማነስ መኖሩ፤
- የንጹህ መጠጥ ውኃ ሽፋን በሚፈለገው ልክ ተደራሽ አለመሆኑ፤
- የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን፤
- የግብርና ግብአት አቅርቦት እጥረት እና የዋጋ ከጊዜ ወደጊዜ መጨመር እንዲሁም የማህበረሰቡ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ወይም ኮሚፖስት አዘጋጅቶ የመጠቀም ልምዱ ዝቅተኛ መሆን።

4.1.3. መልካም አጋጣሚዎች

- አብዛኛው የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባል ሴክተሮች እስከ ቀበሌ መዋቅር ድረስ አስፈጻሚ ያላቸው መሆኑ፤
- የጤናና የትምህርት ተደራሽነትና ሽፋን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ መምጣቱ፤
- ስለሴት ልጆች ትምህርት የማህበረሰቡ ግንዛቤ እያደገ መምጣቱ፤
- ስለተፋሰስ ልማት የማህበረሰቡ ግንዛቤ እያደገ መምጣቱ፤
- በትምህርት ቤቶች የሥነ-ሕዝብ ክበባት እየተጠናከሩ መምጣታቸውና ትምህርት ቤቶች ክበባትን ለማቋቋምና ተማሪዎችም በሥነ-ሕዝብ ክበባት ለመታቀፍ ያላቸው ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ፤
- የማህበረሰብ ሚዲያ በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች ተደራሽ እየሆነ መምጣቱ፤

4.1.4 ሥጋቶች

- የአየር ንብረት መዛባት፣ የአካባቢ ሙቀት መጨመርና የሰብል ምርታማነት መቀነስ፤
- ከሴቶችና ህጻናት አንጻር አሁንም ያልተቀረፉ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች መኖራቸዉ።
- የዋጋ ንረት ለኢኮኖሚ አለመረጋጋትና ለኑሮ ውድነት መስፋፋት ተጽዕኖ ማሳደሩ፤
- የሥራ ፈላጊ ቁጥር መጨመርና ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት መጨመር፤

❖ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ መዘናጋት መፈጠሩ

ክፍል አምስት

5.ዓላማ፣ ስትራቴጂክ ጉዳዮች፣ ግቦችና የማስፈጸሚያ ስልቶች

የቀጣይ አምስት ዓመት (2018 ዓ.ም--2022 ዓ.ም) የሥነ-ህዝብ ፕሮግራም ሰነድ ዓላማ የክልሉን የህዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔ ከክልሉ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት ምጣኔ እንዲሁም ከክልሉ የተፈጥሮ ሀብት ልማት አጠቃቀም ጋር በማጣጣም በሂደት የሕብረተሰቡን የኑሮ ደረጃና አጠቃላይ ደህንነት እንዲሻሻል ማድረግ ነው፡፡

5.2. ስትራቴጂክ ግቦች

1) የክልሉን የሕዝብ ዕድገት ምጣኔ ከኢኮኖሚያዊ ዕድገት ምጣኔ ጋር ማጣጣም፣
2) በከተማና ገጠር የተፈጥሮ አካባቢን በመጠበቅና በማልማት ለነዋሪ ጽዱና ምቹ ማድረግ
3) የግብርና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ ዋስትና በቤተሰብ ደረጃ ማረጋገጥ፤
4) የክልሉ ሕብረተሰብ ፍትሀዊና ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኝ ማስቻል፤
5) የተወልዶ ጤናና አጠቃላይ የህብረተሰቡ የጤና አጠባበቅ ጥራት ማሳደግ፤
6) ሴቶች፣ወጣቶችና ልዩ ድጋፍ የሚሹ ህብረተሰብ ክፍሎች በኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ጉዳይ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል፣

5.3. ስትራቴጂክ ግቦችና ዝርዝር ተግባራት

ግብ.1. የክልሉን የሕዝብ ዕድገት ምጣኔ ከኢኮኖሚያዊ ዕድገት ምጣኔ ጋር ማጣጣም.

ዝርዝር ተግባራት

- የክልሉ የህዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔ አሁን ካለበት 3.11 % ወደ 2.4% እንዲቀንስ በየቀበሌው የማህበረሰብ ማቀጣጠያ ሰነድ ላይ ተከታታይነት ያለው ውይይቶች በማድረግ ምጣኔውን መቀነስ፤
- የተለያዩ ብዙሃን መገናኛን በመጠቀም ትምህርታዊ የሬዲዮ ስክሪፕት በማዘጋጀት የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ አጠቃላይ የውልደት መጠን አሁን ካለበት በ2017 ዓ.ም 4.0 በ2022 ዓ.ም ወደ 3 እንዲቀንስ ማስቻል፤
- በተዋልዶ ጤና ዙሪያ ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች እንዲሁም ለሥነ-ሕዝብ ክበብ መሪ መምህራኖችና ተማሪዎች ሥልጠናዎችን በመስጠትና ህብረተሰቡን እንዲያስተምሩ በማድረግ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን አሁን ካለበት 78% በ2022 ወደ 95% ማድረስ፤
- በክልላችን ሥራ አጥነት በአገር ውስጥ የሥራ ስምሪት ድጋፍ እንዲያገኙ ግንዛቤ በመስጠት በሥራ ላይ የሚሰማሩ ዜጎች ቁጥር አሁን ካለበት በ2017 ዓ.ም 52,388 በ2022 ዓ.ም ወደ 317,037 በማሳደግ የሥራ ዕድል በመፍጠር ሥራ አጥነትን መቀነስ፤
- የክልሉ ሥራ-አጥነት ምጣኔ በከተማ አሁን ካለዉ 41.7 በመቶ በ2022 ዓ.ም ወደ 33 በመቶ ማድረስ
- የክልሉ ሥራ-አጥነት ምጣኔ በገጠር በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 77.4 በመቶ በ2022 ዓ.ም 59.9 በመቶ ማድረስ
- የሥራ ፈላጊ ወጣቶች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ በግብርና ዘርፎች የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው በ2017 ዓ.ም ከነበረዉ 24,701 በ2022 ዓ.ም ወደ 131,035 ማድረስ
- የሥራ ፈላጊ ወጣቶች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፎች የሥራ ዕድል የጠፈጠረላቸው በ2017 ዓ.ም ከነበረዉ 8,514 በ2022 ዓ.ም 52,907 ማድረስ
- የሥራ ፈላጊ ወጣቶች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ በአገለግሎት ዘርፎች የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 19,173 በ2022 ዓ.ም 133,091 ማድረስ

- የሥራ ፈላጊ ወጣቶች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ በማዕድን ኢርጅ በውሃ እና በመስኖ ዘርፍ የስራ እድል የተፈጠረላቸዉ በ2017ዓ.ም 10,363 በ2022 65,099 ማሳደግ
- ነባር ጥቃቅንና አነስተኛ ማኑፋክቸርንግ ኢንዱስትሪዎችን ከማጠናከር አሁን ካለዉ 39 በ2022 ዓ.ም 84 ማድረስ
- የክልሉን ብሎም የሀገሪቱን የገቢ ምንጭ ከፍ ለማድረግ የቡናን ምርት በ2017 በጀት ዓመት ምርት መጠን ከነበረበት 242,081.60 ቶን በ2022 ዓ.ም ወደ 512,786 ቶን የቡና ምርት አቅርቦት መጠን አሁን ካለዉ 48,153 ቶን በ2022 ዓ.ም ወደ 91,947 ቶን በማሳደግ የውጭ ምንዛሪ ከፍ በማድረግ የዜጎችን ኢኮኖሚ ማረጋገጥ፤
- ዋና ዋና ቅመማ ቅመም ሰብሎች ምርት መጠን አሁን ካለዉ 124,432 ቶን በ2022 ዓ/ም ወደ 132,122 ቶን የቅ/ቅመም ምርት አቅርቦት ከላበት 56,170 ቶን በ2022 ዓ.ም 109,752 ቶን ከፍ በማድረስ የአርሶ አደሩን የገቢ ምንጭ ከፍ በማድረግ የኑሮ ደረጃ ማሻሻል፤
- ሻይ ምርት አቅርቦት መጠን በ2017 ዓ.ም ካለዉ 6,215 ቶንበ2022 ዓ.ም ወደ 10,188 ቶን በማድረስ የገቢ ምንጭን ማሳደግ፤
- የማህበረሰብ የመስኖ ተጠቃሚነት ሽፋን አሁን ካለዉ 5,294 ሄ/ር በ2022 ዓ.ም ወደ 6,094 ሄ/ር ማሳደግ እንዲሁም በማዕድን ኢርጅ በውሃ እና በመስኖ ዘርፍ ለስራ አጥ ዜጎች የሚፈጠረውን የስራ እድል አሁን ካለዉ 10,363 በ2022 ዓ.ም ወደ 14,820 በማሳደግ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፡፡

ግብ.2. በከተማና ገጠር የተፈጥሮ አካባቢን በመጠበቅና በማልማት፣ለነዋሪ ጽዱና ምቹ ማድረግ

ዝርዝር ተግባራት

- ለህብረተሰቡ የተለያዩ ጥቅም ያላቸው ችግኞችን በመትከል ክልላዊ የደን ሽፋን አሁን ካለበት 43.85 በመቶ በ2022 ዓ.ም 49.85 በመቶ ማድረስ

- በደን ልማትና ጥበቃ ከሚከናወኑ ተግባራት ተጠቃሚና ተሳታፊ የሆኑ ወጣቶችና ሴቶችን ቁጥር አሁን ካለዉ 15,299 በ2022 ዓ.ም 64,277 ማድረስ
- ችግኞችን በመንከባከብ የፅድቀት መጠን አሁን ካለበት 88 በመቶ በ2022 ዓ.ም 90 በመቶ ማድረስ
- ዘላቂ የአካባቢ አያያዝን በማጎልበት ከባቢያዊ የአየር ብክለት የሚከሰትባቸውን ቦታዎች በመለየት ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ አሁን ካለዉ 202 በ2022 ዓ.ም 383 ማድረስ
- በገጠር እና በከተማ የውሃ ተቋማትን በመገንባት ንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋንን በ2017 ዓ.ም ካለዉ 42.6 በመቶ በ2022 ዓ.ም 55.58 በመቶ በማሳደግ ህዝቡን የንፁህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ
- አማራጭ ኢነርጅ ቴክኖሎጂ ለህ/ተሰቡ ተደራሽ በማድረግ የክልሉን ህዝብ ተጠቃሚ ለማድረግ በ2017 ዓ.ም ካለዉ 120,540 በ2022 ዓ.ም 627,715 ማድረስ
- የአረንጓዴ አጽዋት ሽፋን በሁሉም ከተሞች አሁን ከደረሰበት 24.67 በመቶ በማሳደግ በ2022 ዓ.ም ወደ 36.96 በመቶ በማድረስ ከተሞችን አረንጋዴ ጽዱ ለነዋሪዉ ምቹ ማድረግ፤
- በከተሞች ጽዳት ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ ከማዋል አኳያ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢነተርፕራይዝ እንድደራጁ በማድግ የስራ እድል የተፈጠረላቸዉ ዜጎች አሁን ካለወ 485 በ2022 ወደ 11,127 ማድረስ
- ደረቅ ቆሻሻን ወደ ኦርጋኒክ ቆሻሻ በመቀየር መልሶ ጥቅም ላይ እንድዉል ለማድረግ አሁን ያለዉን 9.86 በመቶ በ2022 ዓ.ም 14.5 በመቶ ማሳደግ፤
- የመኖርያ ቤት ጥያቄን በከተሞች ለመፍታት ማህበረሰቡን በህብረት ስራ ማህበራት በማደራጀትና የህብረተሰቡን የቤት ተጠቃሚነት ለማሳደግ አሁን ካለዉ 601 በ2022 ዓ.ም ወደ 5,567 ማድረስ፤

ግብ.3. የግብርና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ ዋስትና በቤተሰብ ደረጃ ማረጋገጥ፤

- የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በ2017 ዓ.ም ካለዉ 677,634 ሄ/ር በ2022 ዓ.ም 785,120 በማድረስ የምግብ ዋስትናን በቤተሰብ ደረጃ ማረጋገጥ፤
- የሰብል ምርት በበልግና በመኽር አሁን ካለበት በየአመቱ በአማካይ በ7.7% በማሳደግ ምርትና ምርታማነትን አሁን ካለዉ 18,676,797 ሚ/ኩ/ል በ2022 ዓ.ም 28,164,167 በማድረስ የኢኮኖሚ ዕድገትን ማረጋገጥ፣
- የሆርቲካልቸር ሰብሎች ምርትና ምርታማነት አሁን ካለዉ በሄክታር 170 ኩ/ል በ2022 ዓ.ም ወደ 195 ኩ/ል በማሳደግ የነፍስ ወከፍ ገቢን እና የኑሮ ዉድነትን በማረጋጋት የአርሶ አደሩን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል
- የተፋሰስ ልማት ስራዎችን በማስፋፋት የተፋሰስ ልማት አሁን ካለበት 213,187 ሄ/ር በ2022 ዓ.ም ወደ 397,553 ሄ/ር በማሳደግ የአከባቢን ስነ-ምህዳር በመጠበቅ የግብርናን ምርታማነት ማሳደግ ፤
- በበጋ መስኖ ስራ የተለያዩ የዉሃ አማራጮችን በመጠቀም አርሶ እና አርብቶ አደሮች የበጋ መስኖ ስራ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል በ2017 ዓ.ም ከነበረዉ 5,017 በሄ/ር በ2022 ዓ.ም ወደ 6,630 በማስፋት ተጠቀሚነትን ማረጋገጥ
- የኤክስቴሽን ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ቁጥር አሁን ከነበረበት 1,206,552 በ2022 ወደ 1,348,687 በማሳደግ አርሶ አደሮችን የኤክስቴሽን ተጠቃሚነትን ማድረግ
- የክልሉን እንስሳት ሀብት በመጠቀም የሥጋ ምርትን አሁን ካለበት 69,459 በቶን በ2022 ዓ.ም ወደ 108,956 ቶን ማድረስ

ግብ 4 የክልሉ ሕብረተሰብ ፍትሀዊና ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኝ ማስቻል፤

ዝርዝር ተግባራት

- ከ9-12 ያለዉ የክፍል ተማሪ ጥምርታ በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 1፡45 በ2022 ዓ.ም ወደ 1፡40 መቀነ፤

- የቅድመ አንደኛ ትምህርት ቤቶችን ማስፋፋት (ተደራሽነት)በ2017 ዓ.ም ካለዉ 154 ትምህርት ቤቶች በ2022 ዓ.ም ወደ 214 ማሳደግ
- የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ማስፋፋት (ተደራሽነት) አሁን ካለዉ 1568 በ2022 ዓ.ም ወደ 1628 ማድረስ፤
- የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ማስፋፋት (ተደራሽነት) በ2017 ዓ.ም ካለዉ 184 ትምህርተ ቤቶች በ2022 ዓ.ም ወደ 194 ማሰደግ
- የቅድመ አንደኛ ደረጃ ተማሪ- መምህር ጥምርታን ከማሻሻል በ2017 ዓ.ም ካለዉ 1፡130 በ2022 ዓ.ም 1፡50 ማድረስ
- ከ1-8 ኛ ክፍል የተማሪ መምህር ጥምርታ አሁን ካለዉ 1፡67 በ2022 ዓ.ም 1፡50 በማድረስ ስታንዳርዱን ማስጠበቅ
- ከ9-12 ኛ ክፍል የተማሪ መምህር ጥምርታ በ2017 ዓ.ም ካለዉ 1፡247 በ2022 ዓ.ም ወደ 1፡92 መቀነስ
- ደረጃ 3 የደረሱ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሁን ካለዉ 0 በ2022 ዓ.ም 6 ማድረስ
- ደረጃ 3 የደረሱ የአንደኛና የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሁን ካለዉ 86 ትምህርት ቤቶች በ2022 ዓ.ም ወደ 146 ማሳደግ
- ደረጃ 3 የደረሱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2017 ዓ.ም ካለዉ 16 ትምህርት ቤቶች በ2022 ዓ.ም 72 ማሳደግ
- የጥቅል የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የተሳትፎ ምጣኔ አሁን ካለዉ 35 በመቶ በ2022 ዓ.ም ወደ 60 በመቶ ማድረስ
- የጥቅል የአንደኛ ደረጃ (1-6) ትምህርት የተሳትፎ ምጣኔ አሁን ካለዉ 62.8 በመቶ በ2022 ዓ.ም ወደ 100 ማድረስ
- የጥቅል የመካከለኛ ደረጃ (7-8) ትምህርት የተሳትፎ ምጣኔ አሁን ካለዉ 55.2 በመቶ በ2022 ዓ.ም 90 በመቶ ማድረስ
- የንጥር የአንደኛ ደረጃ (1-6) ትምህርት የተሳትፎ ምጣኔ አሁን ካለዉ 55.9 በመቶ በ2022 ዓ.ም 75 በመቶ ማድረስ

- ንጥር የመካከለኛ ደረጃ (7-8) ትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ በ2017 ዓ.ም ካለዉ 39.1 በመቶ በ2022 ዓ.ም ወደ 60 በመቶ መሳደግ
- ጥቅል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (9-12) የተሳትፎ ምጣኔ አሁን ካለዉ 23.8 በመቶ በ2022 ዓ.ም ወደ 41 በመቶ ማድረስ
- ንጥር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (9-12) የተሳትፎ ምጣኔ አሁን ካለዉ 18.2 በመቶ በ2022 ዓ.ም ወደ 35 በመቶ ከፍ ማድረግ
- የስርአተ ጾታ ምጥጥን 1-6ኛ ክፍል አሁን ካለዉ 0.88 በ2022 ዓ.ም 1፡1ማድረስ
- የስርአተ ጾታ ምጥጥን 7-8ኛ ክፍል አሁን ካለዉ 1፡1 በ2022 ዓ.ም ምጥጥኑን ማስጠበቅ
- የስርአተ ጾታ ምጥጥን 9-12ኛ ክፍል አሁን ካለዉ 1፡12 በ2022 ዓ.ም 1፡1 ማድረስ
- የቅድመ አንደኛ ደረጃ መጻህፍት ተማሪ ጥምርታ አሁን ካለዉ 0 በ2022 ዓ.ም 1፡1 ማድረስ
- ለቅድመ አንደኛ ደረጃ የመምህር መምሪያ ጥምርታ አሁን ካለዉ 0 በ2022 ዓ.ም 1፡1 ማድረስ
- የመጀመሪያ ደረጃ መጻህፍት ተማሪ ጥምርታ በ2017 ዓ.ም ካለዉ 1፡6 1፡5 በ2022 ዓ.ም 1፡1 ማድረስ
- የመጀመሪያ ደረጃ የመምህር መምሪያ ጥምርታ አሁን ካለዉ 1፡1 በ2022 ዓ.ም ጥምርታዉን ማስጠበቅ
- የመካከለኛ ደረጃ መጻህፍት ተማሪ ጥምርታ በ2017 ዓ.ም ካለዉ 1፡8 በ2022 ዓ.ም 1፡1 ማድረስ
- የመካከለኛ ደረጃ የመምህር መምሪያ ጥምርታ በ2022 ዓ.ም 1፡1 ማድረስ
- የሁለተኛ ደረጃ መጻህፍት ተማሪ ጥምርታ አሁን ካለበት 1፡1 በ2022 ዓ.ም ማስጠበቅ
- የሁለተኛ ደረጃ የመምህር መምሪያ ጥምርታ አሁን ካለዉ 1፡1 በ2022 ዓ.ም ማስጠበቅ

የጎልማሶች መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም የማንበብና መፃፍ የሚችሉ የተሳታፊዎች አሁን ካለዉ 58,895 በ2022 ዓ.ም ወደ 300,000 ማሳደግ

ግብ.5. የተዋልዶ ጤናና አጠቃላይ የህብረተሰቡን የጤና አጠባበቅ በጥራት ማሳደግ፤

- ከጤና ስታንዳርድ አኳያ በክልሉ ያሉ አጠቃላይ ሆስፒታል ከተገልጋይ ህዝብ ጋር ያለውን ጥምርታ በ2017 ዓ.ም ካለዉ 1፡901,795 በ2022 ዓ.ም ወደ 1፡600,000 መቀነስ
- ከጤና ስታንዳርድ አኳያ በክልሉ ያሉ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል ከተገልጋይ ህዝብ ጋር ያለውን ጥምርታ አሁን ካለዉ1፡300,598 በ2022 ዓ.ም ወደ1፡180359 በመቀነስ የአገልግሎት ሽፋንን ማሳደግ፤
- በክልሉ ያሉ ጤና ጣቢያዎች ከተገልጋይ ህዝብ ጋር ያለውን ጥምርታ አሁን ካለዉ 1:27121 በ2022 ዓ.ም 1፡25000 ማሳደግ ስታንዳርዱን ማስጠበቅ፤
- በክልሉ ያሉ ጤና ኬላዎች ከተገልጋይ ህዝብ ጋር ያለውን ጥምርታ አሁን ካለዉ1፡4803 በ2022 ዓ.ም ወደ1፡4000 በመቀስ የአገልግሎት ሽፋንን ማሳደግ፤
- ሁሉንም አይነት ክትባት ያገኙ ህጻናት ሽፋን በ2017 ዓ.ም ካለዉ 85 በመቶ በ2022 ዓ.ም 95 በመቶ ማሳደግ ጤናማና ሀገር ተረካቢ ህጻናትን ማፍራት፤
- የእናቶች የቅድመ ወሊድ ክትትል ከ12 ሳምንት በፊት ያገኙ ነፍሰ ጡር እናቶች ሽፋን አሁን በ2017 ዓ.ም ካለዉ 13% በ2022 ዓ.ም ወደ 60% ማሳደግ፤
- የድህረ ወሊድ ክትትል አገልግሎት ያገኙ እናቶች ሽፋን አሁን ካለዉ 73 በመቶ በ2022 ዓ.ም 98 በመቶ ማሳደግ
- የእናቶችን በሰለጠነ ባለሙያ የታገዘ የወሊድ አገልግሎት ሽፋን ካለዉ 53% በ2022 ዓ.ም 95% ማድረስ፤
- ከአንድ አመት በታች ህጻናት ሞት መጠን ለመቀነስ በ2017 ዓ.ም ካለዉ 47/1000 በ2022 ዓ.ም ወደ 20/1000 እንዲቀንስ ማስቻል፤
- ከአምስት አመት በታች የህጻናት ሞት መጠን ለመቀነስ አሁን ካለዉ 76/1000 በ2022 ዓ.ም 35/1000 እንዲቀንስ በማስቻል የህጻናትን ሞት መጠን መቀነስ፤

- አዲስ በኤች.አይ.ቪ የሚያዙ ሰዎችን መጠን በ2017 ዓ.ም ካለዉ 0.073/10,000 በ2022 ዓ.ም <1/10,000 እንዲቀንስ ማስቻል
- የጤና አገልግሎት ሽፋን በጤና ጣቢያ አሁን ካለዉ 94% በ2022 ዓ.ም 100% ማድረስ፤
- የጤና አገልግሎት ሽፋን በመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 37% በ2022 ዓ.ም ወደ 56% ከፍ ማድረግ፤
- የጤና አገልግሎት ሽፋን በአጠቃላይ ሆስፒታል በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 85% በ2022 ዓ.ም ወደ 100% ማድረስ፤

ግብ.6. ሴቶች፣ ወጣቶችና ልዩ ድጋፍ የሚሹ በኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ጉዳይ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል፣

ዝርዝር ተግባራት

- ፍልሰት ላይ ያተኮረ የአቻ ለአቻ የህይወት ክህሎት ውይይት ፕሮግራም ሽፋን አሁን ካለዉ 64 በመቶ ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ተጋላጭነትን በ2022 ዓ.ም 30 በመቶ መቀነስ
- ከሴት ልጅ ግርዛት ያለእድሜ ጋብቻ እና ከጎጂ ልማዳዊ ድርግቶች ነፃ የሆኑ ቀበሌዎች ሽፋንን በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 52 በ2022 ዓ.ም 251 ማድረስ፤
- የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ከማሳደግ አንፃር በየደረጃው በሚገኙ ምክር ቤቶች አስፈፃሚ የሴቶችን ተሳትፎ 50 በመቶ ለማድረስ አሁን ካለዉ 15.41 በመቶ በ2022 ዓ.ም 40 በመቶ ማድረስ ሴቶች ውሳኔ ሰጪ እንዲሆኑ ማስቻል፤
- ህግ ተርጓሚ አካላት ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎ 50 በመቶ ለማድረስ አሁን ካለዉ10 በመቶ በ2022 ዓ.ም 22 በመቶ ማሳደግ፤
- የገጠር የመሬት ባለቤትነት የተረጋገጠላቸው ሴቶች ድርሻን በ2017 ዓ.ም ከነበረበት 82,940 በ2022 ዓ.ም ወደ 226,686 በማሳድግ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸዉን ማረጋገጥ

- የሴቶችን የስራ ጫና ለማቃለል ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ ቴክኖሎጅዎችን በማስተዋወቅ ሴቶችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማድረግ አሁን ካለዉ 57,026 ተጠቃሚ በ2022 ዓ.ም ወደ 65,151 ማሳደግ፤
- በከተማ የስራ ዕድል ፈጠራ በንግድና በአገልግሎት ዘርፍ የሴቶችን ኢኮኖሚዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ በ2017 ዓ.ም ከነበረዉ 54,852 በ2022 ዓ.ም 158,065 ማድረስ፤
- ህፃናት ደህንነታቸው ተጠብቆ ትምህርታቸውን እንዲማሩ ከህፃናት ጥቃትና መድሎዎ ነፃ የሆኑ ት/ቤቶች ምጣኔን ለማሳደግ አሁን ካለዉ 206 ት/ቤቶች በ2022 ዓ.ም ወደ 397 ማድረስ፤
- ወሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ላደረጉ ዜጎች የተሃድሶ አገልግሎት በመስጠትና በማቋቋም አሁን ካለዉ 180 በ2022ዓ.ም 331 በማድረስ የማህበራዊ ቀወሶችን መቀነስ፤
- ለአካል ጉዳተኞች የሥነ ልቦናና ማህበራዊ ተሃድሶ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ለማስቻል በ2017 ዓ.ም ከነበረዉ 5,140 በ2022 ዓ.ም ወደ 6,901 በማድረስ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳታፊነታቸውንና ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ
- በአደንዛዥ ዕጽ ጉዳትና አሉታዊ መጤ ልማዳዊ ድርግቶች ላይ ወጣቶች ያላቸውን ግንዛቤ ከመመፍጠር በ2017 ዓ.ም ከነበረዉ 734,952 በ2022 ዓ.ም ወደ 1,176,994 በማሳደግ ከችግር የተጠቁ ወጣቶችን ምጣኔ መቀነስ፤
- ፍልስት ላይ ያተኮረ የአቻ ለአቻ እና የህይወት ክህሎት ውይይት ፕሮግራምን ሽፋን አሁን ካለዉ 90,733 በ2022 ዓ.ም ወደ 145,804 በማሳደግ ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ተጋላጭነትን መቀነስ፤
- በአነስተኛ ገቢ ለሚተዳደሩ ሰዎች ከህብረተሰቡ የኑሮ ደረጃና አቅም ጋር የሚሄድ ወጪ ቆጣቢ ቤቶች እንዲገነቡ ለማድረግ በ2017 ዓ.ም ከነበረዉ 43 ቤቶች በ2022 ዓ.ም ወደ 226 በማሳደግ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ፤
- የሚመለከታቸውን አካላትን በማስተባበር የደሃ ደሃ ቤት አቅርቦትን በማሳደግ በድህነት እና የቤት ዕጦት ላሉ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን በ2017 ዓ.ም ካለዉ 251 ቤቶች በ2022 ዓ.ም ወደ 1,281 በማድረስ፤

5.4 የማስፈጸሚያ ስልቶች

- የተቀናጀ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ተግባራዊ በማድረግ፤
- የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮችን በየደረጃው ያሉ ሴክተር መስሪያ ቤቶች የልማት ዕቅዶቻቸው ውስጥ እንዲያካትቱ በማድረግና እንዲተገብሩ በመከታተል፤
- የሥነ-ሕዝብ ፕሮግራም ሰነድ ክክልል እስከ ወረዳ እንዲገመገም በማገዝ፤
- የሥነ-ሕዝብ ሥራዎችንና ዓላማዎችን ለሕብረተሰቡ ለማስተዋወቅ፣ ለማስተማርና ለመቀስቀስ እንዲሁም የአመራር አካላትን የማሳመን (Advocacy) ሥራዎችን በማከናወን፤
- የኤሌክትሮኒክስና የሕትመት ሚዲያዎችን፣ የስብሰባ መድረኮችንና የማህበረሰብ ውይይት ፕሮግራሞችን በመጠቀም፤
- በየደረጃው ለሚገኙ የሥነ-ህዝብ የሥራ ክፍል የቴክኒክ፣ የቁሳቁስና የፋይናንስ አቅም በመገንባት፤
- የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎቶችን በመብት መርህ መሰረት በማስፋፋት፤
- የክትባት መርሃግብር ፕሮግራሞችን በማስፋፋት፤
- የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችን በማስፋፋት፤
- የኤች አይ ቪ መከላከያዎችን በማጠናከር፤
- የህብረተሰብ አቀፍ ስርዓተ ምግብ ፕሮግራሞችን ማስፋፋት፤
- በየአካባቢው የመምህራን፤የመመሪያ መጽሓፍት እና የመማሪያ ክፍል እጥረትን በመቅረፍ የትምህርት ጥራትን በማሻሻል፤
- ሥርዓተ ትምህርቱን በየደረጃው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመደገፍ፤ ከዘላቂ ልማት፣ ክልላዊና ሀገራዊ ሃላፊነትና ተግባራት ጋር እንዲገናዘብ በማድረግ፤
- የእርሻ መሬትን፣ የሰው ጉልበትንና ቴክኖሎጂን በአግባቡ በመጠቀም፤
- ከተለያዩ የአግሮ-ኢኮሎጂ ዞኖች ጋር የተጣጣመና የተቀናጀ የልማት አቅጣጫ በመከተል፤
- ማሕበረሰቡን በማንቀሳቀስና የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎችን በማፋጠን፤

- ከግብርና ውጪ የሆኑ ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎችን በማስተዋወቅ እንዲስፋፋ ማድረግ፤
- የግብርና ግብዓቶች እንዲቀርቡ በማድረግ፤
- የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓትን በመዘርጋት የሥራ ገበያ ማስተካከያ እርምጃዎች በመውሰድ፤
- የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ አገልግሎትን በማስፋፋት፤
- ለጥቃት፣ ለመገለል፣ ለአድልዎና ለበደል ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የሕግ ጥበቃ እና የማህበራዊ አገልግሎት ድጋፍ የሚሰጡ ተቋማትን በማጠናከር፤
- ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመርና በማስፋፋት፤

5.5 ክትትልና ግምገማ

የዕቅድ አፈጻጸም ክትትል በዕቅድ አፈጻጸም ዙሪያ መረጃ ማሰባሰብ ማደራጀት፣ መተንተንና ለውሣኔ መጠቀምን ያጠቃልላል። የዕቅድ ክትትል ሥራ በአመታዊ የድርጊት መርሃ-ግብር ላይ ተመርኩዞ በወቅታዊ ሪፖርቶች፣ በመስክ ጉብኝትና በውይይት አማካይነት የሚካሄድ ሲሆን ዓላማውም በዕቅድ አፈጻጸም ወቅት በታዩ ችግሮች ላይ በወቅቱ የማስተካከያ ዕርምጃ እንዲወሰድባቸው በማድረግ አፈጻጸሙ የተሳካ እንዲሆን ማድረግ ነው።

በመሆኑም ይህንን የ5 ዓመት የሥነ-ህዝብ ፕሮግራም ሰነድ አፈጻጸም ለመከታተል፣ ለመገምገምና እንደአስፈላጊነቱ የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችል አጠቃላይ እና ዝርዝር ሥርዓትን ይዘረጋል። ከዚህ በተጨማሪ በዕቅድ አስፈጻሚ እና ፈፃሚ አካላት ዘንድ የግልፀኝነትና የተጠያቂነት አሰራርን በማስፈን ድክመቶች እንዲታረሙና ጥንካሬዎች እንዲጎለብቱ ይደረጋል።

ይህም የሚረጋገጠው በፕሮግራም ዘመኑ የየሴክተሩን አመታዊ የአፈጻጸም ሪፖርቶች በማዘጋጀት እና ለሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት በማቅረብ በየአመቱና በፕሮግራም ዘመኑ

የመጨረሻ አመት ሊደረስባቸው የሚገባ ውጤቶችን ለመለካት የሚያስችሉ የክትትል፣ የግምገማና የማረጋገጫ አመላካቾች አንጻር የሚዘጋጁ ይሆናሉ፡፡

በየደረጃው በሚገኙ የአስተዳደር መዋቅሮች ማለትም በክልል፣ በዞኖች፣ በወረዳዎችና በከተማ አስተዳደር ባሉ የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች የፕሮግራሙን አፈፃፀም በቅርበት የሚከታተሉ ሲሆን የክትትልና ግምገማ ሥራዎች በሚከተለው ሁኔታ የሚካሄድ ይሆናል፡፡

- የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች በሥነ-ሕዝብ ጉዳይ ፈጻሚ ሴክተር መስሪያ ቤቶች የልማት ዕቅድ ውስጥ ተካተው እንዲተገብሩ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፡፡
- በዓመት ሁለት ጊዜ (በየግማሽ ዓመቱ) የፕሮግራም ሰነዱን ክትትልና የአፈጻጸም ሪፖርት ለሥነ-ህዝብና ልማት ዳይሬክቶሬት ያቀርባሉ፡፡
- በክልል የሚገኙ የሥነ-ህዝብ ጉዳይ ፈፃሚ መስሪያ ቤቶች እና የዞን የሥነ-ሕዝብ የሥራ ክፍል በየግማሽ ዓመቱ በሚልኩት ሪፖርት ላይ በመመስረት የክልሉ ሥነ-ሕዝብና ልማት ዳይሬክቶሬት ድጋፍ ክትትል ያደርጋል እንዲሁም ግብረ-መልስ ይሰጣል፡፡
- በፕሮግራም ዓመቱ ሁለት ጊዜ ከክልል ፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ጋር በጋራ በመሆን የተመረጡ ዞኖች፣ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች የመስክ ላይ የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ይደረጋል፡፡
- በየዓመቱ አንድ ጊዜ የክልልና የዞን ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት አባላት የሚሳተፉበት ክልል አቀፍ የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ጉባኤ ይካሄዳል፤
- በመጨረሻው ዓመት አፈጻጸሙ በክልሉ ህብረተሰብ ዘንድ ስላስገኘው ውጤት/ፋይዳ የዳሰሳ ጥናት የሚካሄድና ሪፖርት ለሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት የሚቀርብ ይሆናል፡፡

ስትራቴጅክ ግቦችና ዋና ዋና ዝርዝር ተግባራት ድርጊት መረሃ-ግብር

ትምህርት ቢሮ

ተ.ቁ	መለኪያ (KPI) የውጤት አመላካች	መለኪያ	የ2017 መነሻ	2018	2019	2020	2021	2022
1	የክፍል ተማሪ ጥምርታከ1-8ኛ በሬሾ	በሬሽዮ	1:41	1:41	1:41	1:41	1:41	1:41
2	የክፍል ተማሪ ጥምርታከ9-12ኛ በሬሾ	በሬሽዮ	1:45	1:40	1:40	1:40	1:40	1:40
3	ቅድመ አንደኛ ትምህርት ቤቶችን ማስፋፋት (ተደራሽነት)	በቁጥር	154	190	196	202	208	214
4	አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ማስፋፋት (ተደራሽነት)	በቁጥር	1568	1580	1592	1604	1616	1628
5	ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ማስፋፋት (ተደራሽነት)	በቁጥር	184	186	188	190	192	194
6	ቅድመ አንደኛ ደረጃ ተማሪ መምህር ጥምርታን ማሻሻል	በሬሽዮ	1:130	1:80	1:70	1:60	1:55	1:50
7	ተማሪ መምህር ጥምርታ ከ1ኛ-8ኛ ማሻሻል	በሬሽዮ	1:67	1:63	1:59	1:56	1:53	1:50
8	ተማሪ መምህር ጥምርታ ከ9ኛ-12ኛ ማሻሻል	በሬሽዮ	1:247	1:216	1:185	1:154	1:123	1:92
9	ደረጃ 3 የደረሱ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በቁጥር	በቁጥር	0	6	6	6	6	6

10	ደረጃ 3 የደረሱ የአንደኛና የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በቁጥር	በቁጥር	86	12	12	12	12	12
11	ደረጃ 3 የደረሱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በቁጥር	በቁጥር	16	11	11	11	11	12
12	ጥቅል የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የተሳትፎ ምጣኔ በመቶኛ	በመቶኛ	35.6	40	45	50	55	60
13	ጥቅል የአንደኛ ደረጃ (1-6) ትምህርት የተሳትፎ ምጣኔ በመቶኛ	በመቶኛ	62.8	70	77	84	91	100
14	ጥቅል የመካከለኛ ደረጃ (7-8) ትምህርት የተሳትፎ ምጣኔ በመቶኛ	በመቶኛ	55.2	62	69	76	83	90
15	ንጥር የአንደኛ ደረጃ (1-6) ትምህርት የተሳትፎ ምጣኔ በመቶኛ	በመቶኛ	55.9	60	64	68	72	75
16	ንጥር የመካከለኛ ደረጃ (7-8) ትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ በመቶኛ	በመቶኛ	39.1	44	48	52	56	60
17	ጥቅል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (9-12) የተሳትፎ ምጣኔ በመቶኛ	በመቶኛ	23.8	28	31	34	37	41
18	ንጥር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (9-12) የተሳትፎ ምጣኔ በመቶኛ	በመቶኛ	18.2	22	25	28	31	35
19	የስርአተ ጾታ ምጥጥን1-6ኛ ክፍል	በሬሾዮ	0.88	1፡1	1፡1	1፡1	1፡1	1፡1
20	የስርአተ ጾታ ምጥጥን 7-8ኛ ክፍል	በሬሾዮ	1፡1	1፡1	1፡1	1፡1	1፡1	1፡1

21	የስርአተ ጾታ ምጥጥን 9-12ኛ ክፍል	በሬሾ	1፡12	1፡1	1፡1	1፡1	1፡1	1፡1
22	የቅድመ አንደኛ ደረጃ መጻህፍት ተማሪ ጥምርታ	በሬሾ	0	1፡5	1፡4	1፡3	1፡2	1፡1
23	ለቅድመ አንደኛ ደረጃ የመምህር መምሪያ ጥምርታ	በሬሾ	0	1፡5	1፡4	1፡3	1፡2	1፡1
24	የመጀመሪያ ደረጃ መጻህፍት ተማሪ ጥምርታ	በሬሾ	1፡6	1፡5	1፡4	1፡3	1፡2	1፡1
25	የመጀመሪያ ደረጃ የመምህር መምሪያ ጥምርታ	በሬሾ	1፡1	1፡1	1፡1	1፡1	1፡1	1፡1
26	የመካከለኛ ደረጃ መጻህፍት ተማሪ ጥምርታ	በሬሾ	1፡8	1፡5	1፡4	1፡3	1፡2	1፡1
27	የመካከለኛ ደረጃ የመምህር መምሪያ ጥምርታ	በሬሾ	0	1፡5	1፡4	1፡3	1፡2	1፡1
28	የሁለተኛ ደረጃ መጻህፍት ተማሪ ጥምርታ	በሬሾ	1፡1	1፡1	1፡1	1፡1	1፡1	1፡1
29	የሁለተኛ ደረጃ የመምህር መምሪያ ጥምርታ	በሬሾ	1፡1	1፡1	1፡1	1፡1	1፡1	1፡1
30	የጎልማሶች መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም የማንበብና መፃፍ የተሳታፊዎች ብዛት በቁጥር	በቁጥር	58895	60000	60000	60000	60000	60000

	ሥራና ክህሎት ቢሮ							
31	በክልሉ ሥራ አጥነትን ከመቀነስ አንፃር በሀገር ውስጥ የስራ ስምሪት ድጋፍ ቋሚ የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጎች ቁጥርን ማሻሻል	በቁጥር	52,388	57,377	60,245	63,257	66,419	69,739
32	የክልሉ ሥራ-አጥነት ምጣኔ በከተማ	በመቶኛ	41.7	38.8	36	35	34	33
33	የክልሉ ሥራ-አጥነት ምጣኔ በገጠር	በመቶኛ	77.4	73.5	69.5	66.3	63	59.9
34	የሥራ ፈላጊ ወጣቶች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ በግብርና ዘርፎች የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው	በቁጥር	24,701	23,714	24,900	26,145	27,452	28,824
35	የሥራ ፈላጊ ወጣቶች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፎች የሥራ ዕድል የጠፈጠረላቸው	በቁጥር	8,514	9,576	10,054	10,557	11,085	11,635
36	የሥራ ፈላጊ ወጣቶች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ በአገለግሎት ዘርፎች የሥራ ዕድል የጠፈጠረላቸው	በቁጥር	19,173	24,087	25,291	26,555	27,882	29,276
37	ነባር ጥቃቅንና አነስተኛ ማኑፋክቸርንግ ኢንዱስትሪዎችን ማጠናከር	በቁጥር	39	46	54	63	73	84
38	ፍልሰት ላይ ያተኮረ የአቻ ለአቻ የህይወት ክህሎት ውይይት ፕሮግራም ሽፋን በማሳደግ ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ተጋላጭነትን መቀነስ በመቶኛ	በመቶኛ	64	60	56	50	40	30

	ደንና አካባቢ ጥበቃና አየር ንብር ለዉጥ							
39	ለህብረተሰቡ የተለያዩ ጥቅም ያላቸው ችግኞችን በመትከል ክልላዊ የደን ሽፋን አሁን ካለበት ማሳደግ	በመቶኛ	43.85	44.85	45.85	46.83	47.85	49.85
40	በደን ልማትና ጥበቃ በሚከናወኑ ተግባራት ተጠቃሚና ተሳታፊ የሆኑ ወጣቶችና ሴቶችን ቁጥር ማሳደግ	በቁጥር	15299	25094	34889	44685	54481	64277
41	ችግኞችን በመንከባከብ የፅድቀት መጠን ከነበረበት ከፍ እንዲል ማድረግ	በመቶኛ	88	88	88	89	90	90
42	ዘላቂ የአካባቢ አያያዝን በማጎልበት ከባቢያዊ የአየር ብክለት የሚከሰትባቸውን ቦታዎች በመለየት ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ	በቁጥር	202	262	288	317	348	383
	ውሃ ማዕድንና ኢነርጅ ቢሮ							
43	በገጠር እና በከተማ የውሃ ተቋማትን በመገንባት ንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋንን በማሳደግ ህዝቡን የንፁህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ማድረግ	በመቶኛ	42.6	44.95	47.43	50.99	53..09	55.58

44	የማህበረሰብ የመስኖ ተጠቃሚነት ሽፋን ማሳደግ	በቁጥር	5,294	5,730	5,830	5918	6,006	6,094
45	በማዕድን ኢርጅ በውሃ እና በመስኖ ዘርፍ ለስራ አጥ ዜጎች የሚፈጠረውን የስራ እድል ማሳደግ	በቁጥር	10,363	10,880	12,430	13120	13,849	14,820
46	አማራጭ ኢነርጅ ቴክኖሎጂ ለህ/ተሰቡ ተደራሽ በማድረግ የክልሉን ህዝብ ተጠቃሚ ማድረግ	በቁጥር	120,540	132,530	121,040	122540	124,550	127,055
	ከተማ ልማት ኮንስትራክሽን ቢሮ							
47	በአነስተኛ ገቢ ለሚተዳደሩ ሰዎች ከህብረተሰቡ የኑሮ ደረጃና አቅም ጋር የሚሄድ ወጪ ቆጣቢ ቤቶች እንዲገነቡ በማድረግ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ	በቁ/ር	43	40	42	45	48	51
48	የሚመለከታቸውን አካላትን በማስተባበር የደሃ ደሃ ቤት አቅርቦትን በማሳደግ በድህነት እና በቤት ዕጦት ላሉ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን በቅድሚያ እንዲያገኙ ማመቻቸት	በቁ/ር	251	210	231	254	279	307
49	የመኖርያ ቤት ጥያቄን በከተሞች ለመፍታት ማህበረሰቡን በህብረት ስራ ማህበራት በማደራጀትና የህብረተሰቡን የቤት ተጠቃሚነት ማሳደግ	በቁ/ር	601	967	1020	1071	1224	1285

50	የአረንጓዴ እጽዋት ሽፋን በሁሉም ከተሞች አሁን ከደረሰበት በማሳደግ ከተሞችን አረንጋዴ ጽዱ ለነዋሪዉ ምቹ ማድረግ	በመቶኛ	24.67	26.592	29.184	31.776	34.368	36.96
51	በከተሞች ጽዳት ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ ከማዋል አኳያ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢነተርፕራይዝ እንድደራጁ በማድግ የስራ እድል የተፈጠረላቸዉ ዜጎች	በቁ/ር	485	1822	2005	2206	2426	2668
52	ደረቅ ቆሻሻን ወደ ኦርጋኒክ ቆሻሻ በመቀየር መልሶ ጥቅም ላይ እንድዉል ማድረግ	በመቶኛ	9.86	10	11.58	12.5	13.75	14.5
	ግብርና ቢሮ							
53	አጠቃላይ የቡና ምርት መጠን ማሳደግ	በቶን	242,081.60	346,396	348,316	371,611	438,499	512,786
54	የቡና ምርት አቅርቦት መጠንማሳደግ	›› ››	48,153	71,400	74,200	79,554	84,328	91,947
55	አጠቃላይ የቅ/ቅመም ምርት ማሳደግ	›› ››	124.432	125,923	126,887	127,235	128,356	132,122
56	የቅ/ቅመም ምርት አቅርቦት ማሳደግ	›› ››	56,170	65,162	68,540	75,086	95,349	109,752
57	ሻይ ምርት አቅርቦት መጠን ማሳደግ	›› ››	6,215	7,063	7,210	8,329	9,703	10,188

58	የግብርና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ ዋስትና በቤተሰብ ደረጃ ማረጋገጥ፤	በሄ/ር	677,634	722,682	748,950	767,674	775,350	785,120
59	የሰብል ምርት በበልግና በመኽር አሁን ካለበት በየአመቱ በአማካይ በ7.7% በማሳደግ ምርትና ምርታማነትን በማፋጠን የኢኮኖሚ ዕድገታችንን ማረጋገጥ፣	ሚ/ኩ/ል	18,676,797	21,841,448	24,686,374	26,100,908	27,137,267	28,164,167
60	የሆርቲካልቸር ሰብሎች ምርትና ምርታማነት በማሳደግ የወጭ ሚንዛሪን ከፍ በማድረግ የነፍስ ወከፍ ገቢን እና የኑሮ ዉድነትን በማረጋጋት የአርሶ አደሩን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል	ኩ/ል/ሄ/ር	170	173	176	182	189	195
61	የተፋሰስ ልማት ስራዎችን በማስፋፋት የተፋሰስ ልማት አሁን ካለበት በማሳደግ የአከባቢን ስነ-ምህዳር በመጠበቅ የግብርናን ምርታማነት ማሳደግ	በሄ/ር	213,187	272,250	312,911	344,202	378,622	397,553
62	በጋ ስንዴ መስኖ ስራ የተለያዩ የዉሃ አማራጮችን በመጠቀም አርሶ እና አርብቶ አደሮች የበጋ መስኖ ስራ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል	በሄ/ር	5,017	5,778	6,135	6,442	6,500	6,630
63	የኤክስቴሽን ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ቁጥር ከነበረበት በማሳደግ አርሶ አደሮችን የኤክስቴሽን ተጠቃሚ ማድረግ	በቁጥር	1,206,552	1,284,789	1,309,120	1,315,665	1,322,243	1,348,687
64	የክልሉን እንስሳት ሀብት በመጠቀም የሥጋ ምርትን አሁን ካለበት ማሳደግ	በቶን	69,459	88,498	95,517	101,981	106,820	112,161

	ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ							
65	ከሴት ልጅ ግርዛት ያለእድሜ ጋብቻ እና ከጎጂ ልማዳዊ ድርግቶች ነፃ የሆኑ ቀበሌዎች ሽፋንን ማሳደግ	በቁጥር	42	52	58	64	70	77
66	በየደረጃው በሚገኙ ምክር ቤቶች አስፈፃሚ የሴቶችን ተሳትፎ 50 በመቶ ማድረስ	በመቶኛ	15.41	29	33	35	37	40
67	ህግ ተርጓሚ አካላት ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎ 50 በመቶ ማድረስ	በመቶኛ	10	22	22	22	22	22
68	የገጠር የመሬት ባለቤትነት የተረጋገጠላቸው ሴቶች ድርሻን ማሳደግ	በቁጥር	82,940	141,121	155,233	218,540	222,558	226,686
69	የሴቶችን የስራ ጫና ለማቃለል ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ ቴክኖሎጅዎችን በማስተዋወቅ ሴቶችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ	በቁጥር	57,026	58,566	60,147	61,771	63,439	65,151
70	በከተማ የስራ ዕድል ፈጠራ በንግድና በአገልግሎት ዘርፍ የሴቶችን ኢኮኖሚዊ ተጠቃሚነት ማሳደግ	በቁጥር	54,852	107,960	118,756	130,632	143,695	158,065
71	ህፃናት ደህንነታቸው ተጠብቆ ትምህርታቸውን እንዲማሩ ከህፃናት ጥቃትና መድሎዎ ነፃ የሆኑ ት/ቤቶች ምጣኔን ማሳደግ	በቁጥር	206	223	328	345	379	397

72	ወሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ላደረጉ ዜጎች የተሃድሶ አገልግሎት በመስጠትና በማቋቋም የማህበራዊ ቀወሶችን መቀነስ	በቁጥር	180	198	259	281	305	331
73	ለአካል ጉዳተኞች የሥነ ልቦናና ማህበራዊ ተሃድሶ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ በማስቻል የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳታፊነታቸውንና ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ	በቁጥር	5,140	5,679	5962	6,260	6,573	6,901
74	በአደንዛዥ ዕጽ ጉዳትና አሉታዊ መጤ ልማዳዊ ድርግቶች ላይ ወጣቶች ያላቸውን ግንዛቤ በማሳደግ ከችግር የተጠበቁ ወጣቶችን ምጣኔ ማሳደግ	በቁጥር	734,952	803,903	884,293	972,723	1,069,995	1,176,994
75	ፍልስት ላይ ያተኮረ የአቻ ለአቻ እና የህይወት ክህሎት ውይይት ፕሮግራምን ሽፋን በማሳደግ ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ተጋላጭነትን መቀነስ	በቁጥር	90,733	99,586	109,545	120,499	132,549	145,804
76	በተዋልዶ ጤና እና ኤች አይ ቪ /ኤድስ /ዙርያ ግንዛቤ በመፍጠር የተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ወጣቶችን ምጣኔ ማሳደግ	በቁጥር	318,082	347,129	381,842	420,026	462,029	508,232
	በጤና ቢሮ							
77	ከጤና ስታንዳርድ አኳያ በክልሉ ያሉ አጠቃላይ ሆስፒታል ከተገልጋይ ህዝብ ጋር ያለውን ጥምርታ ማሳደግ	ስታንዳርድ	1;901795	1;721436				1;600000

78	ከጤና ስታንዳርድ አኳያ በክልሉ ያሉ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል ከተገልጋይ ህዝብ ጋር ያለውን ጥምርታ ማሳደግ	ስታንዳርድ	1;300598	1;240478		1;212187		1;180359
79	በክልሉ ያሉ ጤና ጣቢያዎች ከተገልጋይ ህዝብ ጋር ያለውን ጥምርታ ማሳደግ	ስታንዳርድ	1:27121					1;25000
80	በክልሉ ያሉ ጤና ኬላዎች ከተገልጋይ ህዝብ ጋር ያለውን ጥምርታ ማሳደግ	ስታንዳርድ	1;4803			1;4500		1;4000
81	የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ አጠቃላይ የወሊድ መጠን እንዲቀንስ ማስቻል	ቁጥር	4					3
82	የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን አሁን ካሉበት ማሳደግ	በመቶኛ	66%	72%	79%	86%	92%	95%
83	ሁሉንም አይነት ክትባት ያገኙ ህጻናት ሽፋን ማሳደግና ጤናማና ሀገር ተረካቢ ህጻናትን ማፍራት	በመቶኛ	85%	87%	89%	91%	93%	95%
84	የእናቶች የቅድመ ወሊድ ክትትል ከ12 ሳምንት በፊት ያገኙ ነፍሰ ጡር እናቶች ሽፋን ማሳደግ	በመቶኛ	13%	29%	36%	43%	52%	60%
85	የድህረ ወሊድ ክትትል አገልግሎት ያገኙ እናቶች ሽፋን ማሳደግ	በመቶኛ	73%	78%	83%	88%	93%	98%
86	የእናቶችን በሰለጠነ ባለሙያ የታገዘ የወሊድ አገልግሎት ሽፋን ማሳደግ	በመቶኛ	53%	61%	69%	78%	86%	95%

87	ከአንድ አመት በታች ህጻናት ሞት መጠን እንዲቀንስ ማስቻል	በቁጥር	47/1000					20/1000
88	ከአምስት አመት በታች የህጻናት ሞት መጠን እንዲቀንስ ማስቻልና ሀገር ተረካቢ የሆኑ ህጻናትን ማፍራት	በቁጥር	76/1000					35/1000
89	አዲስ በኤች.አይ.ቪ የሚያዙ ሰዎችን መጠን እንዲቀንስ ማስቻል	በፐርሰን ት	0.073/1000		<1/10000			<1/10000
90	የጤና አገልግሎት ሽፋን በጤና ጣቢያ	በፐርሰን ት	94%					100%
91	የጤና አገልግሎት ሽፋን በመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል	በፐርሰን ት	37%	42%		47%		56%
92	የጤና አገልግሎት ሽፋን በአጠቃላይ ሆስፒታል	በፐርሰን ት	85%			93%		100%